
# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

## 12ኛ ክፍል



የኢፌዲሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# ለመጽሐፉ ሊደረግ ስለሚገባው የአያያዝ ጥንቃቄ




ይህን መጽሐፍ ብዙ ተማሪዎች ስለሚገለገሉበት በጥንቃቄ ሊያዝ ይገባዋል፡፡

የሚከተሉት 10 ነጥቦች መጽሐፉን በጥንቃቄ ይዞ እንዴት መጠቀም እንደሚቻል ሃሳብ ይሰጣሉ፡፡

1. የመጽሐፉን ሽፋን በጠንካራ ወረቀት ወይንም በላስቲክ መሸፈን፡፡
2. መጽሐፉን ርጥበት በሌለበት ደረቅ ቦታ ላይ በጥንቃቄ ማስቀመጥ፡፡
3. መጽሐፉን በቆሻሻ እጅ ያለማገላበጥና ገፆቹን ያለመግለጥ፡፡
4. በመጽሐፉ የሽፋኑንም ሆነ የውስጥ ገፆች ላይ አላስፈላጊ የሆኑ ስዕሎችንና ጽሑፎችን ያለመሳልና ያለመጻፍ፡፡
5. ለመጽሐፉ የገጽ መለያ ወይንም የንባብ ማረፊያ የሆነ እልባት በጠንካራ ክርታስ ሠርቶ መጠቀም እንጂ የቆሙበትን ቦታ ለማስታወስ ገፆቹን ደጋግሞ ያለማጠፍ፡፡
6. ከመጽሐፉ ውስጥ አንድም ገጽ ሆነ ስዕል ገንጥሎ አለማውጣት፡፡
7. መጽሐፉ ቢገነጠል እንኳ በጥንቃቄ መልሶ በማጣበቂያ ማያያዝ፡፡
8. መጽሐፉ ቦርሳ ውስጥ ሲከተት እንዳይታጠፍና እንዳይጨማደድ ጥንቃቄ ማድረግ፡፡
9. መጽሐፉን ለሌላ ሰው በውሰት ሲሰጥ የተዋሰው ሰው በጥንቃቄ እንዲይዝ መንገር፡፡
10. መጽሐፉን በጥንቃቄ መግለጥ፣ ገፆቹ እንዳይገነጠሉና እንዳይወይቡ በጥንቃቄ መያዝ፡፡

# የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ

## የተማሪ መጽሐፍ

# 12ኛ ክፍል


አዘጋጅ፡- ፕሪን ኢንተርናሽናል አማካሪ ድርጅት

ጸሐፊ፡- አቶ ጳውሎስ ካሱ

ቴክኒካል አማካሪዎች፡- ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ፣ አቶ አማረ አያሌው

አርታኢ፡- አቶ የሻው ተሰማ

ምልክት ቋንቋ፡- አቶ አማረ አያሌው

ግራፊክስ ዲዛይን፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

የምልክት ቋንቋ ስዕል፡- አቶ ፍቃደእግዚአብሄር ከበደ

ሌሎች ስዕሎች፡- አቶ አሰፋ ጉታ

አስተባባሪዎች፡- ዶ/ር ጥላዬ ካሣሁን፣ ዶ/ር ተስፋዬ ባሻ፣ አቶ አንድአርጋቸው ደነቀ



የኢ.ፌ.ዲ.ሪ ትምህርት ሚኒስቴር

# መግቢያ

የኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋን (የኢምቋን) ጨምሮ ሁሉም የምልክት ቋንቋዎች ከንግግር ቋንቋዎች የሚለዩባቸው ሁለት ዋና ዋና ባህሪያት አሉ። አንደኛ፣ የምልክት ቋንቋዎች በእጅ የሚሠሩና በዓይን የሚደመጡ ናቸው። ሁለተኛ፣ የምልክት ቋንቋዎች ፊደሎች (የጣት ፊደሎቻቸው) ገና ለጽሑፍ አገልግሎት ከመዋል ደረጃ ላይ አልደረሱም። በአንደኛው የምልክት ቋንቋዎች ባሕርይ ምክንያት ብዙውን ጊዜ የምልክት ቋንቋ መማሪያ መጽሐፍ በጽሑፍ ሳይሆን፣ በተንቀሳቃሽ ፊልም መልክ (ቪድዮ) ቢዘጋጅ ይመረጣል። ይህ ግንዛቤ ቢኖርም፣ በአሁኑ ጊዜ በሀገራችን ባለው የአቅምና የልምድ ውስንነት ምክንያት፣ ትምህርቱን በቪድዮ ለማዘጋጀት አልተቻለም። ስለዚህ ለጊዜው ትምህርቱን በጽሑፍ ማዘጋጀት እንደ አማራጭ ተወስዷል። በሌሎች ሀገሮችም ይህ አማራጭ በጥቅም ላይ ሲውል ይታያል።

በሁለተኛው የምልክት ቋንቋዎች ባሕርይ ምክንያትም ምንም እንኳን ኢምቋና አማርኛ ሁለት የተለያዩ ቋንቋዎች ቢሆኑም፣ የኢምቋ የራሱ ሥርዓተ ጽሕፈት ስለሌለው፣ ትምህርቱን የአማርኛ ቋንቋ ሥርዓተ ጽሕፈት በመጠቀም ለማብራራት ተሞክሯል። በዚህ ምክንያት፣ በችኮላ ለሚያየው ሰው መጽሐፉ የአማርኛ መማሪያ መጽሐፍ ሊመስል ይችላል። የፌዴራል መንግስት ዋና የሥራ ቋንቋ አማርኛ ስለሆነ፣ ቋንቋው ለዚህ መጽሐፍ ዝግጅት እንደ መሣሪያ ተመረጠ እንጂ፣ የሥርዓተ ጽሑፍ ባህል ያለው ማንኛውንም የሀገራችንን ቋንቋ መጠቀም ይቻል ነበር። ስለዚህ ይህ የተማሪዎች መማሪያ መጽሀፍ በአማርኛ መዘጋጀቱ የኢምቋ አማርኛ ነው ማለት አይደለም።

ይህን መጽሐፍ አንድ የስፖርት አይነት እንዴት እንደሚሠራ ከሚያብራራ መጽሐፍ ጋር ማመሳሰል ይቻላል። የስፖርት ትምህርት ተግባር ነክ በመሆኑ ከዚህ አይነት መጽሐፍ ተጠቃሚ መሆን የሚቻለው፣ ማብራሪያውን ተከትሎ ተግባሩን በማከናወን ነው እንጂ መጽሐፉን በማንበብ ብቻ አይደለም። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ በዚህ የኢምቋ የተማሪው መማሪያ መጽሐፍ ውስጥ በጽሑፍ የቀረበው ይዘት በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የኢምቋ ትምህርት ምን እንደሆነና እንዴት እንደሚከናወን የሚያብራራ እንጂ ራሱ ትምህርቱ አይደለም። የኢምቋ ትምህርት እንደ ስፖርት ትምህርት ተግባር ነክ በመሆኑ፣ ተማሪው የተፈለገውን የኢምቋ ክሂል ሊያዳብር የሚችለው ማብራሪያውን ተከትሎ ተግባሩን በማከናወን ነው እንጂ፣ መጽሐፉን በማንበብ ብቻ አይደለም። ስለዚህ ተማሪው ጥረት ማድረግ ያለበት ማብራሪያውን ወደ ተግባር በመቀየር ላይ እንዲሆን ይመከራል።

እንደ ማንኛውም ተግባር ነክ ትምህርት፣ በክፍል ውስጥ ንቁ ተሳትፎ ማድረግና ለሚሰጠው ትምህርት የተለየ ትኩረት መስጠት ለተማሪው ስኬታማነት አስፈላጊ ጉዳይ ነው። አለማቋረጥ መለማመድም ለስኬታማነት ወሳኝ ነው። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ብዙ የኢምቋ ሰዋሰው ሥርዓቶችን ለማስተዋወቅ ተሞክሯል። አብዛኞቹ ሰዋሰው ነክ ምሳሌዎች በመጀመሪያ በኢምቋ ይሰጡና፣ ቀጥሎ ትርጉማቸው በአማርኛ ይቀመጣል። የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮችን ከአማርኛ ዐረፍተ ነገሮች ለመለየት የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች በአግድሞሽ እንዲጻፉ ተደርጓል። የመጻፍ ተግባር አስፈላጊ በሆነ ጊዜ የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮች ስር በማስመር ከአማርኛ መለየት ይቻላል።

በተጨማሪም ይህ የተማሪው መጽሐፍ ተማሪው እንዲማር የታቀዱትን ምልክቶች ሥዕል በሙሉ ባለማካተቱ ውጤታማ ለመሆን በኢትዮጵያ መስማት የተሳናቸው ብሔራዊ ማኅበር የተዘጋጀውን የኢምቋ መዝገብ ምልክት ከመጽሐፉ ጋር አብሮ መጠቀም ይመከራል።

አዘጋጁ

**ማውጫ** **ገጽ**

ምዕራፍ አንድ:

የቤተሰብ ሕግ------------------------------------------------------------------------------- 2

ምዕራፍ ሁለት፡

ተግባቦት በኢምቋ --------------------------------------------------------------------------- 16

ምዕራፍ ሦስት፡

የሙስና አስከፊነት --------------------------------------------------------------------------- 26

ምዕራፍ አራት፡

ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ ------------------------------------------------- 37

ምዕራፍ አምስት፡

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት -------------------------------------------------------- 49

ምዕራፍ ስድስት፡

ዓለምአቀፋዊነት ወይስ ብሔራዊነት?----------------------------------------------------- 62

ምዕራፍ ሰባት፡

ሕገወጥ የሰዎች ዝውውር አስከፊ ገጽታ------------------------------------------------ 72

ምዕራፍ ስምንት፡

ራስን ማብቃት------------------------------------------------------------------------------ 85

ምዕራፍ ዘጠኝ፡

የልማድ አሉታዊ ገጽታ --------------------------------------------------------------------- 96

ምዕራፍ አስር፡

የፍልስፍና ሚና---------------------------------------------------------------------------- 110

የክለሳ ጥያቄዎች ------------------------------------------------------------------------------ 122

# ምዕራፍ አንድ

## የቤተሰብ ሕግ




**የሚጠበቁ ውጤቶች:**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ስለቤተሰብ ሕግ ምንነትና አስፈላጊነት በምክንያትና በውጤት አስደግፋችሁ በኢምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ከቤተሰብ ሕግ ጋር የተያያዙ የኢምቋ ምልክቶችን ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው በዕለት ተዕለት ተግባቦት ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- ከምንባቡ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ትለያላችሁ፤
- ከአንድ ምልክት ተጨማሪ ምልክቶችን ትመሠርታላችሁ፤
- ለምልክቶች ተቃራኒ ትሰጣላችሁ፤
- የኢምቋ ግስ ዓይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፤
- የግል ሐሳባችሁን ለመግለፅም ግሶቹን ትጠቀማላችሁ፤
- የግሶቹን ልዩነትነት በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ፤

## ቁልፍ ምልክቶች




ቤተሰብ




ሕግ




ቀለብ



መሠረት




ምሰሶ




ተቋም




ከለላ





እንዲዘልቅ/መዘለቅ




ትዳር



መተግበር



ግላዊ


ተቆጥቧል/መቆጠብ



ሹም


አንቀጽ


ሞራል



ፈቃደኝነት


እውቅና



ወጉ/ወግ


መርሆች/መርህ



እስካልተቃረነ/መቃረን




ቅድመ-ሁኔታ




የፀና/መፅናት




ክልከላዎች



ነክ



ማህበራዊ



መጋጨት



ፍቺ

# ክፍለ ትምህርት አንድ

## የማነቃቂያ ተግባር

### እይታዊ ንባብ

የሚከተለውን ሥእል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ከቤተሰብ ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን በመጠቀም ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ በኢ.ምቋ አስረዱ።



### የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. በአካባቢያችሁ ወይም በባህላችሁ አንድ ወንድና ሴት ለመጋባት ማሟላት የሚጠበቅባቸው መስፈርቶች ምንድናቸው?
2. በአካባቢያችሁ ወይም በባህላችሁ ቤተሰብ እንዳይፈርስ ማሕበረሰቡ የሚከተለውን ሥርአት ለክፍል ጓደኞቻችሁ  በኢ.ምቋ አስረዱ።
3. ጋብቻ በምን መልክ ቢመሠረትና ቢመራ የተሻለ ውጤታማ ይሆናል ብላችሁ ታስባላችሁ?

### ምንባብ

ተማሪዎች፤መምህራችሁ የቤተሰብ ሕግ የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሃሰቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

# የቤተሰብ ሕግ

የአንድ ማኅበረሰብ መሠረት ቤተሰብ እንደሆነ ይታወቃል። ይህ የማኅበረሰብ መሠረት የሆነው ቤተሰብ የሚመሠረተው በተለያየ መልኩ ቢሆንም፣ ዋናው ግን ጋብቻ ነው። ቤተሰብ የኅብረተሰቡ ዋና ምሰሶ በመሆኑ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ተቋም ነው። ይህ ተቋም ከመቋቋሙ አንስቶ እስከ መጨረሻው ድረስ በሕግና ስርዓት መመራት ይኖርበታል። የቤተሰብ መመስርቻ የሆነው ጋብቻ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ኖሮት እንዲዘልቅ ኅብረተሰቡ ባወጣው ሕግ መሠረት መመሥረት ይኖርበታል። በቆይታው ጊዜ የሚፈጠሩት ግንኙነቶችና ውጤቶች እንዲሁ የሕግ ከለላ ሊኖራቸው ይገባል። ለምሳሌ የልጅ አስተዳደግና አስተዳደር፣ በትዳር ውስጥ ስለሚፈጠሩ ንብረቶች፣ ከትዳር በፊት የነበሩ ንብረቶች ጉዳይ በሕግ መመራት ይኖርባቸዋል። በተጨማሪም፣ በባልና ሚስት መሀል የሚፈጠሩ ግንኙነቶች እንዲሁ በሕግ መሠረት መደንገግ ይኖርባቸዋል።

ሰዎች በተለያዩ ምክንያቶች ይህን የኅብረተሰብ ምሰሶ የሆነውን ትዳር ሊያፈርሱት ይችላሉ።ይህ ተቋም መፍረስ ካለበት ህጋዊ በሆነ መልኩ ነው መፍረስ ያለበት። ትዳር ሲፈርስ የራሱ የሆነ ውጤት ይኖረዋል። የልጆች ቀለብ፣ በትዳር ዘመን የተገኙ ንብረቶች አከፋፈል፣ ወዘተ በሕግ መሠረት መሆን ይኖርበታል።

የሀገራችን የቤተሰብ ሕግ የጋብቻን ትርጉም በቀጥታ ከመስጠት ተቆጥቧል። ነገር ግን ከሕጉ የተለያዩ ድንጋጌዎች የቃሉን ትርጉም ማግኘት ይቻላል። ሕጉ የጋብቻን ትርጉም ያላስቀመጠው “ጋብቻ” ለሚለው ቃል ሁሉንም የህበረተሰብ ክፍሎችና ዜጎች ሊያስማማ የሚችል ትርጉም ማስቀመጥ ስለማይቻል ነው። የተሻሻለው የቤተሰብ ሕጋችን በዋነኝነት ለሦስት አይነት የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓቶች እውቅና ሰጥቷል። እነዚህም በክብር መዝገብ ሹም ፊት የሚፈጸም ጋብቻ፣ በኃይማኖት ስርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻና በባህል ስርዓት መሠረት የሚፈጸም ጋብቻ ናቸው። ከዚህ በተጨማሪም የቤተሰብ ሕጉ በውጭ ሀገር የተፈጸመ ጋብቻ በዛ ሀገር ጋብቻ አፈፃፀም ሕግ መሠረት የተፈጸመና የሀገራችንን ባህል የማይቃረን ከሆነ እውቅና ይሰጣል።

ሕጉ ከላይ በተጠቀሱት ሦስት ስርዓቶች ጋብቻ ቢፈጸምም ሦስቱም ዓይነት የጋብቻ መፈጸሚያ ስርዓቶች በቅድሚያ ሊያሟሏቸዉ የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች ይዘረዝራል። ከእነዚህ ቅድመ-ሁኔታዎች መካከል መሠረታዊ የሚባሉት፤ ፈቃደኝነት፣ የተጋቢዎቹ እድሜ፣ ዝምድና፣ በጋብቻ ላይ ጋብቻ እና በብቸኝት ለመኖር የተወሰነ ጊዜ ናቸው።

ተጋቢዎች ሕጉን ጠብቀው እንደተጋቡ ሁሉ፣ ፍቺ የግድ ሲሆን ደግሞ ሕጋዊ በሆነ ሁኔታ መፋታት እንዳለባቸው ደንግጓል። ፍቺውን ተጋቢዎች በስምምነት ማድረግ እንደሚችሉ ወይም በአንዱ ወይም በሁለቱም ተጋቢዎች ጥያቄ እንደሚሆን ሕጉ አስቀምጧል። በተጨማሪም የፍቺው ሕጋዊ ውጤት የእኩልነትን መርህ መሠረት አድርጎ መሆን እንዳለበትም ተገልጿል። በመሆኑም በሕጋዊ መንገድ የተመሠረተው ጋብቻ በሕጋዊ መንገድ መፍረስ አለበት።ይህ ሕጋዊ ፍቺም ሕጋዊ ውጤት አለው።

አንድ ኅብረተሰብ እንደ ኅብረተሰብ ቀጣይነት እንዲኖረው ይፈልጋል። ባህሉ፣ ቋንቋው፣ ስርዓቱ፣ ወጉ ወዘተ ተጠብቆለት እንዲቀጥል የሁሉም ኅብረተሰብ ምኞትና

ፍላጎት ነው። ይህ እንዲሆን ለኅብረተሰቡ ምሰሶ የሆነው ቤተሰብ ልዩ የሕግ ጥበቃ ሊደረግለት ይገባል።

*አንዳልካቸዉ ወርቁ፣ "የጋብቻ እና ፍቺ ህጋዊ ውጤቶች ከተሻሻለው የቤተሰብሕግ አንፃር" ፌስቡክ፣ የካቲት 2007 ዓ.ም.፡ ለምንባብ እንዲመች ተደርጎ የተሻሻለ*

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዟችሁ ታቅደው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በቃል መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢ.ምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢ.ምቋ አንብቡ።
2. የምንባቡን ዋና ዋና ነጥቦች ጥቀሱ።
3. መጽሀፎቻችሁን ሳትመለከቱ የምንባቡን መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ በኢ.ምቋ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢ.ምቋ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢ.ምቋ አቅርቡ።

1. የቤተሰብ መሠረት የሆነው ጋብቻ በኅብረተሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ኖሮት እንዲዘልቅ በምን ሁኔታ መመሥረት አለበት?
2. በጋብቻ ውስጥ የሕግ ከለላ ከሚያስፈልጋቸው ጉዳዮች ውስጥ ሦስት ምሳሌዎች ጥቀሱ።
3. ትዳር ሲፈርስ በሕጋዊ መንገድ መሆን ያለበት ለምንድነው ?
4. የተሻሻለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ የጋብቻን ትርጉም በቀጥታ ያላስቀመጠው ለምንድነው?
5. የተሻሻለው የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ እውቅና የሰጣቸው ለሦስት አይነት የጋብቻ ማስፈፀሚያ ስርዓቶች ምንድናቸው ?
6. በውጭ ሀገር የተፈጸመ ጋብቻ ሕጋዊ እውቅና የሚሰጠው ምን ሲያሟላ ነው?
7. የኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ እውቅና የሰጣቸው የጋብቻ መፈጸሚያ ስርዓቶች በቅድሚያ

ሊያሟሏቸው የሚገቡ ቅድመ ሁኔታዎች ምንድናቸው ?

8. የቤተሰብ ሕጉ እነዚህን ሁሉ ዝርዝር ጉዳዮች ለማካተት የሞከረበት ዋና ምክንያት ምንድነው?

9. በኢትዮጵያ የቤተሰብ ሕግ ፍቺ የሚፈቀደው ጥያቄው ከማን ሲመጣ ነው?

10. የቤተሰብ ልዩ የሕግ ጥበቃ የሚያስፈልገው ለምን እንደሆነ በአጭሩ አስረዱ።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## የምልክት ቋንቋ ግሶች

ግስ ድርጊት (ተግባር) ወይም መሆንን የሚገልጽ የቃል ክፍል ወይም ምልክት ነው። በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ምን እንደተከናወነ የሚያሳየን ቃል ወይም ምልክት ግስ ይባላል። ሁሉም ቋንቋዎች ግስ አላቸው። የኢምቋም ግስ አለው። ሆኖም ድምጽ ከሚጠቀሙ ቋንቋዎች ግስ ጋር ሲነጻጸሩ፣ የኢምቋ ግሶች የተለየ ባህሪ ያላቸው ከመሆኑም በላይ፣ የተወሳሰቡና ከሌሎች የኢምቋ የሥነምልክት ክፍሎች ለመለየት የሚያስቸግሩ ናቸው። የኢምቋ ግሶችን ለየት ከሚያደርጓቸው ባህሪያት ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፤

1. አንድ የኢምቋ ምልክት እንደ አገባቡ ግስ ወይም ስም ሲሆን ይችላል

**ምሳሌ አንድ፤**

1. *መቀመጥ መውደድ አይደለም።* (መቀመጥ አልወድም።)
2. *መቀመጥ የለም።* (መቀመጫ የለም።)

ከላይ ባሉት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ አብሮት ከሚሄደው የፊት ገለጻ በስተቀር የመቀመጥ መሠረታዊ ምልክት ተመሳሳይ ነው። ሆኖም በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ አገልግሎቱ የግስ ሲሆን፣ በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግን አገልግሎቱ ስም ነው። ምልክቱ ተመሳሳይ ቢሆንም የኢምቋ ተጠቃሚዎች ከአገባቡ መረዳት ይችላሉ።

**ምሳሌ ሁለት፤**

1. *ሞት መጥፎ* (ሞት መጥፎ ነው።)
2. *ሞት ፍረሃት* (መሞት ያስፈራል።)

በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ እንደታየው፣ አብሮት ከሚሄደው የፊት ገለጻ በስተቀር የሞት መሠረታዊ ምልክቱ በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ ተመሳሳይ ነው። ይሁንና በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ አገልግሎቱ ስም ሲሆን፣ በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግን ግስ ነው።

2.አንድ ምልክት እንደ አገባቡ ግስ ወይም ቅጽል ሲሆን ይችላል

ምሳሌ አንድ፤

1. *ቆንጆ ቆንጆ ሴት ሴት አየ።* (ብዙ ቆንጆ ሴቶች አየሁ።)

2. ሴት ሴት *ቆንጆ ቆንጆ መውደድ።* (ሴቶች መቆነጃጀት ይወዳሉ።)

ቆንጆ ቆንጆ በአንድም በሁለትም እጅ ሊሰራ የሚችል ምልክት ነው። አብሮት ከሚሄደው የፊት ገለጻ በስተቀር *መሠረታዊ* ምልክቱ ድግግሞሹን ጨምሮ በሁለቱም ዐረፍተነገሮች ውስጥ ተመሳሳይ ነው። ሆኖም በመጀመሪያው ዐረፍተ ነገር ውስጥ አገልግሎቱ ቅጽል ሲሆን፣ በሁለተኛው ዐረፍተነገር ውስጥ ግን ግስ ነው። ግስ ወይም ቅጽል መሆኑን ማወቅ የሚቻለው ከአገባቡ ነው።

**ምሳሴ ሁለት**

1. *መቆም ዝም ጥሩ አይደለም።* (ዝም ብሎ መቆም ጥሩ አይደለም።)

2. *መቆም ነገር የለም።* (ቋሚ ነገር የለም።)

አብሮት ከሚሄደው የፊት ገለጻ በስተቀር በሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የ**መቆም** *መሠረታዊ* ምልክት ተመሳሳይ ነው። ይሁንና በመጀመሪያው ዐረፍ ተነገር ውስጥ አገልግሎቱ ግስ ሲሆን፣ በሁለተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግን ቅጽል ነው። ግስ ወይም ቅጽል መሆኑን ማወቅ የሚቻለው ከአገባቡ ነው።

አንድ ምልክት ብቻውን ሲታይ ግስ፣ ስም ወይም ቅጽል ለሆን ይችላል። ሰለዚህ ብዙውን ጊዜ አንድን ምልክት በማየት ብቻ ግስ ወይም ስም ወይም ቅጽል ነው ለማለት ያስቸግራል። የቃል ክፍሉን ለመናገር አገባቡን ማጥናት አስፈላጊ ነው።

3. **የኢምቋ ግሶች የጊዜ አመልካች ቅጥያ አይቀበሉም**

የኢምቋን እንደ አማርኛ ካሉ ቋንቋዎች ከሚለዩት ባህሪያት አንዱ ግሶቹ የጊዜ አመልካቾችን የማይቀጥሉ መሆኑ ነው። በሥነድምጻዊ ቋንቋዎች የግሶች አንድ ተግባር ጊዜ ማሳየት ነው።

**ምሳሴ**

መብላት የሚለውን የአማርኛ ግስ ብንወስድ፣ የግሱን ፊደላት በመቀያር የክንውኑን ጊዜ እንዲያሳይ ማድረግ ይቻላል፤

| | |
|---|---|
| የወደፊት ክንውን፡ | እበላለሁ |
| ያለፈ ክንውን፡ | በልቻለሁ |
| ገና ያልተከናወነ፡ | አልበላሁም |

እስከዛሬ በተጠኑ የምልክት ቋንቋዎች ውስጥ ግን የምልክት ቋንቋ ግስ የጊዜ አመልካቾችን አይወስድም። ይህም ማለት የጊዜ አመልካቾች በግሱ ላይ አይቀጠሉም ማለት ነው። የኢምቋ ግሶችም ተመሳሳይ ባህሪ እንዳላቸው እስካሁን የተደረጉ ጥናቶች ይጠቁማሉ። በኢምቋ ግሶች ላይ


በአማርኛው “መብላት” ግስ ላይ እንደተደረገው ለማድረግ የቋንቋው ሕግ አይፈቅድም። ቀደም ባሉት ክፍሎች እንደተማራችሁት፣ በኢምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ አንድ ክንውን የተከናወነበትን ወይም የሚከናወንበትን ጊዜ ለማሳየት የሚቻለው በግሱ ላይ ጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን በመቀጠል ሳይሆን፣ እራሱን የቻለ ሌላ ምልክት ከግሱ በፊት ወይም በኋላ በመጠቀም ነው።

**ምሳሌ**

ከላይ የአማርኛ ግስ የጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን ለማሳያት የተጠቀምነውን የ“መብላት”ን የኢምቋ ምልክት  እንደ ምሳሌ ማየት ይቻላል፤

**የመብላት ምልክት**

የወደፊት ክንውን፡ *የመብላት ምልክት* + *በኋላ/ወደፊት* = እበላለሁ



**የመብላት ምልክት +** = **እበላለሁ**

**የወደፊት ክንውን፡** *መብላት በኋላ/ወደፊት* (እበላለሁ)

**ያለፈ ክንውን፡** *መብላት መጨረስ* (በልቻለሁ)

**ያልተከናወነ፡** *መብላት ገና/አይደለም* ( አልበላሁም)

ከላይ እንደ ምሳሌ በተሰጡት ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ እንደሚታየው በግሱ (የመብላት ምልክት ላይ) ላይ ምንም አይነት ቅጥያ አይደረግም። የኢምቋ ግሶች ጊዜ አመልካች ቅጥያዎች ስለማይወስዱም የሚከፋፈሉት ድምጽ የሚጠቀሙ ቋንቋዎች ውስጥ በተለመደው መሠረት  አላፊ ግስ፣ የወደፊት ግስ፣  ወዘተ፣ በማለት አይደለም። ግሶች የሚከፋፈሉት ጊዜን መሠረት አድርገው ሳይሆን ባህሪያቸውን መሥረት አድርጎ ነው።

**የኢምቋ ግሶች በሦስት ይከፈላሉ፤**

1. ግልጽ ግሶች
2. አመልካች ግሶች
3. ገላጭ ግሶች

**ግልጽ ግሶች፤** ቋሚ አቅጣጫና እንቅስቃሴ ያላቸው በሁሉም ዐረፍተነገሮች ውስጥ በተመሳሳይ መንገድ የሚሰሩ ምልክቶች ናቸው።

**አመልካች ግሶች:** እነዚህ ግሶች ቋሚ አቅጣጫና እንቅስቃሴ የሌላቸውና በዐረፍተነገሮች ውስጥ እንዳላቸው አገባብ የሚለዋወጡ ግሶች ናቸው።

**ገላጭ ግሶች:** እነዚህ ግሶች ምስላዊ ሲሆኑ ግሱ እንደሚወክለው ነገር የሚለዋወጡና ቋሚ የሚባል የእጅ ቅርጽም ሆነ አቅጣጫ የሌላቸው ግሶች ናቸው

በቀጣይ ምዕራፎች ውስጥ የሦስቱን ግሶች ምሳሌዎች ከነአጠቃቀማቸው እንመለከታለን።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌ እያስደገፋችሁ በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ

1. የኢምቋ ግሶች ድምጽ ከሚጠቀሙ ቋንቋዎች ግሶች የሚለዩባቸው ዋና ዋና ባህሪያት ምንድናቸው?
2. የኢምቋ ግሶች የጊዜ አመልካች ቅጥያዎችን የማይወስዱት ለምንድነው?
3. የኢምቋ ግሶች በስንት ይከፈላሉ? ምን ምን በመባል? ዘርዝሩ
4. በሦስቱ የኢምቋ ግሶች መካከል ያሉትን ልዩነቶች በአጭሩ አስረዱ
5. የቤተሰብ ሕግ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ለእያንዳንዱ የኢምቋ የግስ አይነት ምሳሌ የሚሆኑ ሦስት ሦስት ግሶች ፈልጋችሁ አሳዩ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ምልክቶች እንደ አገባባቸው ግስ ወይም ስም ሊሆኑ ይችላሉ። ከላይ በምሌዎቹ ውስጥ እንዳያችሁት ግስ ወይም ስም ሊሆኑ እንደሚችሉ በኢምቋና በአማርኛ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳዩ።

1. ማሽተት

2. ማየት
3. መስማት
4. መሽናት
5. መሸጥ

## መልመጃ ሦስት

የቤተሰብ ሕግ ከሚለው ምንባብ ለእያንዳንዱ የኢ.ምቋ ግስ ምሳሌ የሚሆኑ ሦስት ሦስት ግሶችን ለይታችሁ አሳዩ።

ምሳሌ:

| | ግስ | አይነት |
|---|---|---|
| 1. | መመሥረት | ግልጽ ግስ |
| 2. | የሚሰጠው | አመልካች ግስ |
| 3. | አስተዳደግ | ገላጭ ግስ |

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ከስሞች ቅጽል ምልክቶችን መመሥረት

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ሲሆኑ ስም ናቸው። በቃላቱ ከተወከሉት ስሞች ቅጽል ምልክቶች በመፍጠር በክፍል ውስጥ አሳዩ።

ምሳሌ፤

የስም ምልክት- ሀገር

የሀገር ቅጽል - የሀገራዊ ምልክት፡ (ሀገር + የ ዊ ማሳያ)

ሀገር ስም- ሀገራዊ ቅጽል

1. ባህል

2. ሕግ
3. እኩል
4. ዘመን
5. ፍትህ

## ክፍለ ትምህርት አራት

### የኢምቊ፡ ሰዋሰው ናሙናዎች ልምምድ

**ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹የቤተሰብ ሕግ›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቊ አንብቡ።**

1. **ኢምቊ:** *ማሕበረሰብ መሠረት ምን- ቤተሰብ ይሂ በደንብ ማወቅ ሁሉም።*

   **አማርኛ:** የአንድ ማኅበረሰብ መሠረት ቤተሰብ እንደሆነ ይታወቃል።

2. **ኢምቊ:** *ቤተሰብ ትኩረት ከፍተኛ መስጠት ምክንያት ምን- ሕብረተሰብ ድጋፍ ዋና ያ።*

   **አማርኛ:** ቤተሰብ የህበረተሰቡ ዋና ምሰሶ በመሆኑ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ተቋም ነው።

3. **ኢምቊ:** *ሌላ ሀገር ተመሳሳይ ኢትዮጵያ ሕግ ቤተሰብ አለ።*

   **አማርኛ:** በኢትዮጵያም የቤተስብ ሕግ አለ።

4. **ኢምቊ:** *ሀገር የእኛ ሕግ ቤተሰብ መጋባት ምን-ምን ማብራራት መስጠት የለም፣ ዝም።*

   **አማርኛ:** የሀገራችን የቤተሰብ ሕግ የጋብቻን ትርጉም በቀጥታ ከመስጠት ተቆጥቧል።


5. **ኢምቊ:** *ሀገር የእኛ ሕግ ቤተሰብ- አዲስ ተሻሻለ - ሦስት መጋባት*

*መመሥረት መንገድ ማወቅ መስጠት።*

**አማርኛ:** የተሻሻለው የቤተሰብ ሕግ በዋነኝነት ለሦስት አይነት የጋብቻ ማስፈጸሚያ ስርዓቶች እውቅና ሰጥቷል።

# ምዕራፍ ሁለት

## ተግባቦት በኢምቋ




**የሚጠበቁ ውጤቶች**

ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤


- የተግባቦትን ምንነትና  የተግባቦት ክፍሎችን ታስረዳላችሁ፤
- ከተግባቦት ጋር የተያያዙ የኢምቋ ምልክቶችን ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው ታሳያላችሁ፤
- በኢምቋ ተግባቦት ውስጥ ወሳኝ የሆኑትን ሦስት ክሂሎች በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ፤
- በኢምቋ የመግባባት ብቃታችሁን ታሳድጋላችሁ ፤
- ግልጽ የሚባለውን የመጀመሪያውን የኢምቋ ግስ አጠቃቀም በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ፤
- ግልጽ ግሶችን በእለትተእለት ተግባቦቶች ውስጥም ትጠቀማላችሁ፤
- ሀገር በቀል ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ከነትርጉማቸው በኢምቋ ታቀርባላችሁ፤
- ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በንግግራችሁ ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- ከሚሰጡ የኢምቋ ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶችን ትመሠርታላችሁ፤
- በሚሰጣችሁ ርዕስ ዙሪያ ስራአት ጠብቃችሁ በመወያየት ማጠቃለያ ሃሳብ ላይ ትደርሳላችሁ።


## ቁልፍ ምልክቶች



ተግባቦት



መግባባት


ንግግር



መረዳት


መጋራት/የጋራ



ስሌት


ማሽን



መልእክት ላኪ/ተናጋሪ




ክህሎት




መልእክት መላክ



ስነ-ምልክት



መልእክት ተቀባይ/አድማጭ



ማኅበረሰብ

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### የማነቃቂያ ተግባር

### እይታዊ ንባብ

1. የሚከተሉትን ምስሎች በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ በኢምቋ አስረዱ።
2. ከሁለቱ ምስሎች ሰላማዊ ተግባቦት የሚያሳየው የትኛው እንደሆነ በማስረጃ አስደግፋችሁ ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢምቋ አስረዱ። ሰላማዊ ወይም ሰላማዊ ያልሆነ ተግባቦት ያላችሁበትን ምክንያት አብራሩ።



## የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ብዙውን ጊዜ መስማት የተሳናቸው በቤት ውስጥ፣ በአካባቢያቸው፣ በትምህርት ቤት ወዘተ የኢምቋ በደንብ ከማይችሉ ሰዎች ጋር በኢምቋ ለመግባባት ሲሞክሩ ችግሮች ያጋጥሟቸዋል። በዚህ ነጥብ ዙሪያ ያላችሁን ገጠመኝ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።
2. መስማት የተሳናቸው የኢምቋ በደንብ ከማይቸሉ ሰዎች ጋር በኢምቋ ለመግባባት ሲሞክሩ ችግሮች የሚያጋጥሟቸው ለምን ይመስላችኋል? በምሳሌ አስደግፋችሁ አብራሩ።

## ምንባብ

### ተግባቦት በኢምቋ

ተግባቦት በሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ቁልፍ ቦታ ያለው ጉዳይ ነው። የሁሉም ነገሮች መሠረት ነው። ያለ ስኬታማ ተግባቦት ሰዎች በጋራ ሊኖሩም ሆነ ሊሰሩ አይችሉም። የተግባቦትን ምንነት ሁሉንም አንባቢ ሊያስማማ በሚችል መልኩ ማስረዳት ያስቸግራል። ተግባቦት በሁለት አካላት መካከል መልእክት መቀባበልና መላላክን ያካትታል። ይህን ተግባራዊ ለማድረግ ደግሞ ሁለቱም አካላት የሚጋሩት ቋንቋ ሊኖር ይገባል። ቋንቋ ሲባል ግን የግድ በድምጽ ላይ ብቻ የተመሠረተ ቋንቋ ማለት አይደለም። ተግባቦት በሰውና በሰው፣ በሰውና በእንስሳት፣ በሰውና በማሽኖች፣ በማሽኖችና በማሽኖች፣ ወዘተ፣ መካከል ሊከወን ይችላል። ሁለትና ከሁለት በላይ የሆኑ አካላት በጋራ ቋንቋ ለመግባባት ሁሉም በተግባቦት ውስጥ የሚሳተፉ አካላት በጋራ የተስማሙበትና የተቀበሉት ስርዓት ሊኖር ይገባል። ተግባቦት ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ተጋባቢዎቹ የሚግባቡበት ቋንቋ ክሂሎት ሲኖራቸው ነው።እነዚህን ክሂሎትም በሦስት መክፈል ይቻላል፤ የቋንቋው ሥነልሳናዊና ባህላዊ ባህሪያት ግንዛቤ፤ በማዳመጥ መረዳትና፣ በቋንቋው ሀሳብን ማስተላለፍ ናቸው።

በኢትዮጵያ ምልክት ቋንቋ (የኢምቋ) መግባባት የሚቻለውም የተግባቦቱ ተሳታፊዎች ማለትም፤ መልእክት አፍላቂውና ተቀባዩ እነዚህ ክሂሎች ሲኖሯቸው ነው። የኢምቋን መሠረት በማድረግ ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ክሂሎች ማብራራት ይጠቅማል። አንደኛው ተፈላጊ ችሎታ የኢምቋ ሥነምልክታዊና ባህላዊ ባህሪያት

ግንዛቤ ነው። ይህ ግንዛቤ የኢምቋ ምልክቶች እውቀትን የሚያጠቃልል ቢሆንም ስኬታማ ተግባቦት መፍጠር ምልክቶችን ከማወቅ በላይ የሆነ ግንዛቤ የሚጠይቅ ክሂል ነው። የኢምቋ ግንዛቤ መስማት በተሳናቸው ባህል ተቀባይነት ባለው መንገድ ንግግር የመጀመር፣ እንዳይቋረጥ የማድረግ፣ የመቀጠልና የማስፋፋት ክሂሎችን ያጠቃልላል። ከዚህ በተጨማሪም አንድ ሰው የኢምቋ ግንዛቤ አለው ለማለት ተናጋሪው አድማጩ መረዳቱን የማጣሪያና አስፈላጊ ሲሆንም ማብራሪያ የመጠየቂያ ዘዴዎች ክሂሎት ሊኖረው ይገባል።

ሁለተኛው ተፈላጊ ክሂል ኢምቋ የመረዳት ክሂል ነው። ይህም የተግባቦቱ አካል የሆነው ሰው የሚጠቀምባቸውን የተግባቦት ዘዴዎች በአግባቡ ተቀብሎና ተርጉሞ መልእክቱን የመረዳት ክሂል ነው። በኢምቋ ተግባቦት ሂደት ውስጥ ኢምቋ የመረዳት ክሂል ዘጠኝ ንዑስ ክሂሎችን ያጠቃልላል። እነዚህ ንዑስ ክሂሎች፤ የቦታ አጠቃቀምን፣ የምልክቶችን እርባታን፣ የጣት ፊደላት በዓይን ማንበብን፣ በእጅ የማይሰሩ የኢምቋ ክፍሎችን መረዳትን፣ የሰውነት እንቅስቃሴዎችን መተርጎምን፣ የአንድን ምልክት አራት መሠረታዊ ክፍሎችን በአግባቡ መለየትን፣ የምልክቶች አጠቃቀምንና የምሳሌያዊ አነጋገሮች አተረጓጎምን ያጠቃልላል። አንድ ሰው ኢምቋ መረዳት ይቻላል የሚባለው እነዚህ ክሂሎች ሲኖረውና በተግባቦቱ ውስጥ በአግባቡ ተግባራዊ ሲያደርጋቸው ነው።

ሦስተኛው ተፈላጊ ክሂል ራስን በኢምቋ የመግለጽ ችሎታ ነው። ይህ ችሎታ የኢምቋ ምልክቶችን በኢምቋ ሥነምልክታዊ ሥርአት መሠረት በማገጣጠምና ዐረፍተ ነገሮች የመመሥረትና መስማት በተሳናቸው ባህል መሠረት ሀሳብን ማስተላለፍን ያጠቃልላል። ይህ ክሂሎት በሁለተኛው ክሂሎት ስር ከተጠቀሱት ክሂሎች በተጨማሪ እንደ አድማጩና እንደ ሁኔታው የአቀራረቡን ደረጃና አይነት የመቀያየር ክሂሎትን ይጨምራል።

ይህ ተግባቦት በኢምቋ ስኬታማ ሊሆን የሚችለው ተግባቢዎች ቢያንስ ሦስቱ መሠረታዊ ክሂሎች ሲኖራቸው ብቻ ነው።

*ጳውሎስ ካሡ (በ2007 ዓ.ም). የኢትዮጵያ የምልክት ቋንቋ ማስተማሪያ መመሪያ. አአዩ ፕሬስ፣አዲስ አበባ. ለንባብ እንዲመች ተደርጎ የተዘጋጀ*

## መልመጃ አንድ

**የሚከተሉት ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ**

1. በዚህ ምዕራፍ የመጫረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቋ አንብቡ።
2. መጽሀፎቻችሁን ሳትመለከቱ የምንባቡን መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ

ወስጥ በኢ.ምቋ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢ.ምቋ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢ.ምቋ አቅርቡ።

1. ተግባቦት ምን ያካትታል? አብራሩ
2. በሁለት አካላት መካከል ተግባቦትን ተግባራዊ ለማድረግ ሊኖር የሚገባው ዋና ነገር ምንድነው?
3. ቋንቋ ሲባል በድምጽ ላይ ብቻ የተመሰረተ ማለት አይደለም። ይህን አባባል የሚደግፍና ምሳሌ የሚሆን አንድ ቋንቋ ምንድነው?
4. መግባባት የሚችሉ አካላት ምሳሌዎችን ጥቀሱ።
5. ተግባቦትን ስኬታማ ለማድረግ ተጋባቢዎቹ ተግባቢዎቹ ሊኖራቸው የሚገባውን የቋንቋ ክሂሎት ዘርዝሩ
6. የኢ.ምቋ መግባባት የሚቻለው የተግባቦቱ ተሳታፊዎች ምን አይነት ክሂሎች ሲኖራቸው ነው?
7. የኢ.ምቋ ሥነምልክታዊና ባህላዊ ባህሪያት ግንዛቤ ይህ ግንዛቤ ከኢ.ምቋ ምልክቶች እውቀት የሚለየው በምንድነው?
8. አንድ ሰው ኢ.ምቋ መረዳት ይቻላል የሚባለው ምን አይነት ክሂሎች ሲኖሩት ነው?
9. ራስን በኢ.ምቋ የመግለጽ ክሂል ምንድነው?
10. በኢ.ምቋ መግባባትን በተመለከተ በምንባቡ ውስጥ የተጠቀሰና መታረም የሚገባው አመለካከት ምንድነው?

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## የኢምቋ ግሶች (ክፍል ሁለት)

### መልመጃ አንድ

በምዕራፍ አንድ ውስጥ በተማራችሁት መሠረት እንደ አገባባቸው ስም፣ ቅጽል ወይም ግስ ሊሆኑ የሚችሉ አምስት የኢ.ምቋ ምልክቶች ፈልጋችሁ በምዕራፍ አንድ ውስጥ በተሰጠው ምሳሌ መሠረት የተለያየ አገልግሎታቸውን በዓረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳዩ።

### መልመጃ ሁለት

ተግባቦት በኢ.ምቋ ከሚለው ምንባብ ውስጥ አምስት ግልጽ እና አምስት አመልካች ግሶቹን ለይታችሁ በማውጣት በአይነት በአይነታቸው አስቀምጡ።

ምሳሌ፡

ተግባቦት፡ አመልካች ግስ

የተመሠረተ፡ ግልጽ ግስ

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## ምሳሌያዊ አነጋገሮች

ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሥነቃል አንድ ክፍል ናቸው። ምሳሌየዊ አነጋገሮች ደራሲ የሌላቸው ከትውልድ ትውልድ ሲተላለፉ የመጡ የአንድ ማኅበረሰብ ገጠመኞች ጥርቅም ናቸው። ስለዚህ የአንድ ህዝብ የጋራ ሀብት ናቸው። ምሳሌያዊ አነጋገሮች ሰዎች መልእክታቸውን በአጭሩና የሰው ትኩረት በሚስብ መልኩ ለማስተላለፍ የሚጠቀሙበት የአነጋገረ ጥበባት ናቸው። እንደ ንግግር ማጣፈጫም ያገለግላሉ። ሁሉም ማሕበረሰቦችና ቋንቋዎች ምሳሌያዊ አነጋገሮችን ይጠቀማሉ። በአንድ ቋንቋ የተነገረን ምሳሌያዊ አነጋገር በሌላ ቋንቋ ውስጥ ስንጠቀም የሁለተኛውን ቋንቋ ባህላዊ መሠረትና የቋንቋውን ስርአት በተከተለ መልኩ መሆን አለበት። የኢ.ምቋ ተጠቃሚዎች ምሳሌያዊ አነጋገሮችን መጠቀም ይችላሉ። በዚህ ክፍል ውስጥ ከአማርኛ ቋንቋ የተወሰዱ የተወሰኑ ምሳሌያዊ አነጋገሮችን በኢ.ምቋ ማቅረብ በሚቻልበት መንገድ ላይ

ልምምድ እናደርጋለን።

ከታች የተለመዱ የአማርኛ ምሳሌያዊ አነጋሮችና ትርጉማቸው እንዲሁም የኢምቋ ተቀራራቢ ትርጉምና ፍቺ ጎን ለጎን ቀርበዋል። በኢማቋ የቀረበውን ዐረፍተ ነገር በክፍል ውስጥ በኢምቋ በማቅረብ አጠቃቀሙን ተለማመዱ።

1. **ምሳሌያዊ አነጋገር:** *ወዳጅ - ዓይን ሁለቱ ትንሽ ስህተት በቂ።* (ለወዳጅና ለዓይን ትንሽ ይበቃዋል።)

   **ትርጉም:** *ወዳጅ ቅሬታ ስሜት ቀላል ስለዚህ ጥንቅቅ ጥንቅቅ አስፈላጊ።*(ወዳጅ በቀላሉ ስለሚቀየም በጥንቃቄ መያዝ ይገባል።)

2. **ምሳሌያዊ አነጋገር:** *ጨለማ አለ ማብራት፤ መከራ አጋጠም ዘዴ መፈለግ።* (ለጨለማ ጊዜ መብራት፤ለመከራ ጊዜ ብልሀት።

   **ትርጉም:** *ችግር ማስወገድ እንዴት- ጥበብ ጥቅም ዘዴ መፈጠር አስፈላጊ።* (ችግርን ለመቅረፍ ዘዴ መቀየስ ያስፈልጋል)

3. **ምሳሌያዊ አነጋገር:** *ክረምት አለፈ- አለቀ ቤት ሥራ ሥራ ያስፈልጋል አይደለም* (ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም)

   **ትርጉም:** *አንድ ነገር አለፈ በቃ ቁጭት ቅጭት ስህተት* (ያለፈው ነገር መቆጨት አይገባም)

4. **ምሳሌያዊ አነጋገር:** *መሥረቅ ሰው ሱስ ማርካት ማድረግ ምን- አየት አየት ዳቦ እንኳን አገኘ መላስ መላስ ዝም።* (ሌባ ላመሉ ዳቦ ይልሳል።)

   **ትርጉም:** *አንድ ሰው ልማድ አለ መልቀቅ አይደለም ማሰር።* (ልማደኛ ልማዱ አይለቀውም)

5. **ምሳሌያዊ አነጋገር:** *ልብ እሱ ነጭ ማቡካት ማቡካት።* (ልቡ ነጭ ያቦካል።)

   **ትርጉም:** *ምኞት ህልም ብዙ።* (ምኞቱ ሰፊ ነው)

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ምሳሌያዊ አነጋገሮች በክፍል ውስጥ ተወያዩባቸውና ትርጉማቸውን ስጡ።

1. *ቅርንጫፍ ዋና ዛፍ ሁለት ተመሳሳይ* (ቅርንጫፉ እንደዛፉ)
2. *ዱላ ሌላ አቅማጫ፤ ፍየል ሌላ አቅማጫ።* (ቅዝምዝም ወዲያ ፍየል ወዲህ)
3. *ራስ በግ የለም ቀበሮ አውሬ ተመሳሳይ መቁጠር አይደለም።* (በግ የሌለው ቀበሮን አውሬ

አይላትም።)

4. *ችኩል ችኩል ሰው ሰው ቤት ሥራ ግርግዳ ምን- ሳር ረዥም።* (የነቶሎቶሎ ቤት ግርግዳው ሰንበሌጥ።)

5. *ችግር ትንሽ አጋጠም ሰው አደረገ ምን ማግባት እርጉዝ፤ ከባድ ችግር አጋጠመ ሰው አደረገ ምን- መወለድ ሴት ህጻን አብሮ ማግባት።* (የቸገረው እርጉዝ ያገባል፤ የባሰበት እመጫት።)

## መልመጃ ሁለት

### የምልክቶች እርባታ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ ከተወከሉት ምልክቶች አዳዲስ ምልክቶችን በመፍጠር በክፍል ውስጥ አሳዩ። ምልክቶቹ ቅጽል ሲሆኑ የምትፈጥሩት አዲስ ምልክት ስም መሆን አለበት

ምሳሌ፡ ዝናባማ (ቅጽል ምልክት)

*መልስ፡* ዝናብ (ስም)

1. ስኪታማ
2. ትርፋማ
3. ጤናማ
4. ጉረኛ
5. ዳመናማ

## ክፍለ ትምህርት አራት

## የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎች ልምምድ

ከዚህ በታች የተቀመጡት የአማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹ተግባቦት በኢምቋ›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቋ አንብቡ።

1. **ኢምቋ**: *መግባባት ሰው ሕይወት ዋና አስፈላጊ ነገር- ቁልፍ።*

**አማርኛ:** ተግባቦት በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ቁልፍ ቦታ ያለው ጉዳይ ነው።

2. **ኢምቋ:** *ስኬት መግባባት የለም- ሰው መኖር፣ ሥራ አንድ አብሮ አይቻልም።*

**አማርኛ:** ያለ ስኬታማ ተግባቦት ሰዎች በጋራ ሊኖሩም ሆነ ሊሰሩ አይችሉም።

3. **ኢምቋ:** *መግባባት ማለት ምን- ሁለት ሰው ወይም ብዙ አንድ መናገር ሌላ መረዳት እንደገና ሌላ መናገር አንድ መረዳት መቀጠል።*

**አማርኛ:** ተግባቦት በሁለት ወይም ከዛ በላይ በሆኑ አካላት መካከል መልእክት መቀባበልና መላላክን ያካትታል።

4. **ኢምቋ:** *መግባባት መፍጠር መጀመሪያ እሱም እሱም ሁለት ተመሳሳይ ቋንቋ ማወቅ ግድ።*

**አማርኛ:** ተግባቦትን ለመፍጠር ሁለቱም አካላት የሚጋሩት ቋንቋ ሊኖር ይገባል።

5. **ኢምቋ:** *መግባባት ሰው ሰው ብቻ አይደለም ሰው ሌላ ሰው፣ ሰው እንሰሳ፣ ሰው ማሽን፣ ማሽን ሌላ ማሽን ሁለት መቀጠል መቻል።*

**አማርኛ:** ተግባቦት በሰውና በሰው፣ በሰውና በእንሰሳት፣ በሰውና በማሽኖች፣ በማሽኖችና በማሽኖች፣ ወዘተ፣ መካከል ሊከወን ይችላል።

# ምዕራፍ ሦስት

## የሙስና አስከፊነት




**የሚጠበቁ ውጤቶች፡**


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ስለሙሰኝነት ምንነትና አስከፊነት ደረጃውን በጠበቅ ኢ.ምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ከሙሰኝነት ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን በተለያዩ ምሳሌዎች ውስጥ ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው ትጠቀማላችሁ፤
- ሙስኝነትና ሙሰንና መሠረት በማድረግ ተመሳሳይ የአማርኛ ቃላትንና የኢ.ምቋ ምልክታቸውን ግንዱን ከብዜቱ በመለየት ትርጉማቸውን በኢ.ምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ‹‹ግልጽ ግሶች›› የሚባሉትን የኢ.ምቋ ግሶች የኢ.ምቋን ስርአት በተከተለ መንገድ በእለታዊ ተግባቦት ውስጥም መጠቀም ትጀምራላችሁ፤
- እንቆቅልሾችን በኢ.ምቋ ታቀርባላችሁ፤
- እንቆቅልሾች በኢ.ምቋ ሲቀርቡላችሁ ትተረጉማላችሁ።

## ቁልፍ ምልክቶች



ሙስና



አንኳር




ርዕሰ-ጉዳይ




ብልጽግና




አጀንዳዎች



መንሰራፋት



ኮሚሽን



ብልሹ




ድርና ማግ




መረብ




ሙሰኝነት




መዋቅር




ተጽዕኖ ማሳደር




ያንዣበበ/ማንዣበብ



ብዝበዛ



ዘርፍ



ስነ-ምግባር




## የማነቃቂያ ተግባር

## እይታዊ ንባብ

የሚከተለውን ስዕል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።



## የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በፊት ስለሙስና የሰማችሁትንና የምታውቁትን ነገር ለክፍል ጓደኞቻችሁ በኢ.ምቋ አስረዱ።
2. ሙስና በዜጎች ሕይወት ላይ የሚኖረውን አሉታዊ ተጽዕኖ በኢ.ምቋ አስረዱ።

## ምንባብ

ተማሪዎች፤መምህራችሁ የሙስና አስከፊነት የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሃሰቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

## የሙስና አስከፊነት

በዘመናችን በተደጋጋሚ ከሚነገሩ፣ ከሚደመጡ በብዛትም ከሚፃፍባቸው የህዝብና የመንግስት አንገብጋቢ የውይይት አጀንዳዎች መካከል አንዱ "ሙስና" ነው።

የዓለም ባንክ ሙስናን "በህዝብ የተሰጠ ስልጣንን ለግል ብልጽግና መጠቀም" በማለት ይተረጉመዋል። ሙስና ስልጣንን ተገን በማድረግ የህዝብ ንብረቶችን መመዝበርን፣ የዜግነት መብት የሚፈቅደውን አገልግሎት ለመስጠት ጉቦ መቀበልን፣ ለግል ጥቅም ሲሉ ፍትህ ማዛባትን፣ ያልተገባ ጥቅም ማጋበስን... ያጠቃልላል።

ሙስና ለአንድ ሀገርና ህዝብ ህልውና ከፍተኛ ስጋት ነው። ሙስና በተንሰራፋበት ሥርዓት መልካም አስተዳደር ሊሰፍን አይችልም። መልካም አስተዳደር ከሌለ ደግሞ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ይረጋገጣሉ ተብሎ አይታሰብም። ሦስቱም የማይነጣጠሉ ወሣኝ ጉዳዮች ናቸው።

ከሌሎች በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ካሉ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር በሀገራችን የተመዘገበው የሙስና ደራጃ ዝቅተኛ ነው። ያም ሆኖ በሀገራችን እድገት ላይ እያሳደረ ያለው ተጽእኖ ግን ከፍተኛ መሆኑ አይካድም። ከጊዜ ወደ ጊዜም እተባባሰ ነው። በዚህ ምክንያትም በአሁኑ ወቅት በተደጋጋሚ ከሚነገሩ፣ ከሚደመጡ በብዛትም ከሚፃፍባቸው አንኳር የኅዝብና የመንግስት ሰፋፊ የውይይት ርዕሰጉዳዮች አንዱ ሆኗል።

ሙሰኝነት በሁሉም ዘርፎች ውስጥ ያለ ቢሆንም በጣም ጎልቶ የሚታየው ግን ለሀገራችን እድገት ወሳኝ በሆኑና መንግስት ከፍተኛ በጀት በሚመድብላቸው የኢኮኖሚው ዘርፎች ነው። መንግስትም በሀገራችን ሙሰኝነት እንዳለ፣ የሀገር እድገትን፣ መልካም አስተዳደርንና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን በእጅጉ እያዳከመ እንደሆነም አምኖ የተቀበለው እውነታ ነው። አምኖ መቀበል ብቻ ሳይሆን ሙሰኝነትን ከስሩ ነቅሎ ለመጣል የተለያዩ ፕሮግራሞችን ነድፎ መንቀሳቀስ ከጀመረ ቆይቷል።

ሙስና የሀገርን እድገት ከመጉዳት በተጨማሪ የሀገርን ስም ያጠፋል። በጥቂት ስግብግብ ግለሰቦች ምክንያት ሀገራችን በሙሰኝነት ምክንት ስሟ ሲነሳ መስማት ለሁሉም ዜጋ የሚያንገበግብ ጉዳይ እየሆነ ነው። ስለዚህ ሙስናንና ሙሰኞችን በመዋጋትና በአገርና ህዝብ ላይ ያንዣበበን አደጋ በማስወገድ ሂደት ውስጥ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ተሳታፊ መሆን አለበት።

ሙሰኝነት ሊጠፋ የሚችለው እያንዳዳችን ከሙስናና ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ፀድተን፣ ሌሎች ተከታዮቻችንና ተተኪዎቻችንም በዚሁ ፀረሙስና አመለካከት ታንፀው እንዲያድጉ ስናደርግ ብቻ ነው። ሙሰኞችን አለማጋለጥ እራሱ ሙሰኝነት ነው። የሙስና ችግር አስካለ ድረስ ሁላችንም የተጠያቂነት ሀላፊነት አለብን። ሙስናን እያየን ዝም የምንል ከሆነ፣ የሙስና መረብ፣ ድርናማት ሲዘረጋጋ እየተመለከትን እንዳላየን ቸል የምንል ከሆነ የሙሰኝነት ተባባሪ እንሆናለን። ስለዚህ ሙሰኝነትን ለማጥፋት ሁላችንም የየድርሻችንን መወጣት አለብን።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዟችሁ ታቅደው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በቃል መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበባችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቋ አንብቡ።
2. የምንባቡን ጠቅላላ መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢምቋ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢምቋ አቅርቡ።

1. በዓለም ባንክ ትርጉም መሠረት ሙስና ምንድነው?
2. “በህዝብ የተሰጠ ስልጣንን ለግል ብልጽግና መጠቀም” ምን ማለት እንደሆነ አብራሩ
3. ሙስና ለአንድ ሀገርና ህዝብ ህልውና ከፍተኛ ስጋት የሚሆነው ለምንድነው?
4. አሁን በሀገራችን ያለው የሙስና ሁኔታ ምን ይመስላል?
5. በሀገራችን ያለው ሙስና በጣም ጎልቶ የሚታየው በየትኞቹ ዘርፎች ውስጥ ነው?
6. ሙስና የሀገርን እድገት ከመጉዳት በተጨማሪ የሚያስከትለው ችግር ምንድነው?
7. ሙሰኝነት እንዲጠፋ ከእያንዳንዱ ዜጋ የሚጠበቀው ምንድነው?

## መልመጃ ሦስት

### ባዶ ቦታ መሙላት

መምህራችሁ የሚከተሉትን ከምንባቡ ውስጥ የተወሰዱ ዐረፍተ ነገሮች በኢምቋ ከአነበቡላችሁ በኋላ ዐረፍተ ነገሮቹ ውስጥ የጎደሉትን ምልክት/ምልክቶች አሳዩ።

1. ሙስና በተንሰራፋበት ሥርዓት ____________________ ሊሰፍን አይችልም።

2. ከሌሎች በተመሳሳይ የእድገት ደረጃ ላይ ካሉ ሀገራት ጋር ሲነጻጸር በሀገራችን የተመዘገበው____________________ዝቅተኛ ነው።

3. መንግስትም በሀገራችን ሙሰኝነት እንዳለ፣ የሀገር እድገትን፣ መልካም አስተዳደርንና የዲሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታን በእጅጉ እያዳከመ እንደሆነም ____________________ እውነታ ነው።

4. ____________________ሊጠፋ የሚችለው እያንዳንዳችን ከሙስናና ከኪራይ ሰብሳቢነት አስተሳሰብ ፀድተን፣ሌሎች ተከታዮቻችንና ተተኪዎቻችንም በዚሁ ፀረሙስና አመለካከት ታንፀው እንዲያድጉ ስናደርግ ብቻ ነው።

5. የሙስና ችግር አስካለ ድረስ ሁላችንም ____________________ አለብን።

6. ሙሰኞችን አለማጋለጥ እራሱ ____________________ ነው።

# ክፍለ ትምህረት ሁለት

## የኢምቁ ግስ፤ ግልጽ ግሶች

### ግልጽ ግሶች

ቋሚ አቅጣጫና እንቅስቃሴ ያላቸው በሁሉም ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በተመሳሳይ መንገድ የሚሠሩ ግሶች ናቸው።

እነዚህ ግሶች ብዙውን ጊዜ ከማሰብ ጋር የተያያዙ አእምሮአዊ ተግባራት፣ ስሜት ነክና ለውጥ የማያካትቱ ክንውኖች የሚገልጹ ምልክቶችን ያጠቃልላሉ።

**ምሳሌዎች:** መብላት፣ መጠጣት፣መጠበቅ፣ ማሰብ፣ መውደድ፣ ማየት፣ መጥላት፣ ወዘተ

እነዚህ ግሶች በሁሉም ሁኔታ ውስጥ የማይለወጡ ሲሆን ምንም ዓይነት ቅጥያ አይቀበሉም።

**አጠቃቀም:**

1. *አለሚቱ መውደድ* (አለሚቱን እወዳታለሁ።)
2. *አለሚቱ መውደድ* (አለሚቱ ትወደኛለች።)

በሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የመውደድ ምልክት ጉልህ ልዩነት አያሳይም። ማን ማንን እንደወደደ የሚታወቀው ከአገባቡ፣ ከፊት ገለጻና አካላዊ እንቅስቃሴዎች ነው።

1. *መምጣት ድረስ መጠበቅ* (እስክመጣ ድረስ ጠብቀኝ።)

2. *መምጣት ድረስ መጠበቅ* (እስክትመጣ ድረስ እጠብቅሃለሁ።)

ከላይ እንደተገለጸው በሁለቱም ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ የመጠበቅ ምልክት ጉልህ ልዩነት አያሳይም። ማን ማንን እንደሚጠብቅ የሚታወቀው ከአገባቡ፣ ከፊት ገለጻና አካላዊ እንቅስቃሴዎች ነው።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌ እያስደገፋችሁ በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ መልሱ

1. የኢ.ምቋ ግልጽ ግስ ማለት ምን ማለት ነው? ምሳሌዎች ስጡ።
2. የኢ.ምቋ ግልጽ ግሶችን ልዩ መለያዎች አስረዱ።
3. የኢ.ምቋ ግልጽ ግሶች በተለይ ከምን ጋር የተየያዙ ናቸው?

## መልመጃ ሁለት

ከላይ የተሰጡትን ምሳሌዎች መሠረት በማድረግ የሚከተሉት የኢ.ምቋ ግልጽ ግሶች በተለያየ አገባብ ውስጥ እንደማይለወጡ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም አሳዩ።

1. *መብላት*
2. *መጠጣት*
3. ማየት
4. ማሰብ
5. *መጥላት*

## መልመጃ ሦስት

ከምንባቡ ውስጥ አምስት ግልጽ ግሶችን ፈልጋችሁ በማውጣት የራሳችሁን የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮች *መሥርቱ*።

ምሳሌ፡

ግልጽ ግስ፡ የሚነገሩ/መናገር

ዐረፍተነገር፡ መስማት መሳን መናገር መከልከል አይደለም

# ክፍለ ትምህርት ሦስት

## እንቆቅልሽ

እንቆቅልሾች ግራብማጋባት ላይ የተመሠረቱ ቃላዊ ግጥሚያዎች ናቸው። እንደ መዝናኛም እንደ መማሪያም ያገለግላሉ። የዚህ ክፍለ ትምህርት ዓላማ እንቆቅልሾችን በኢምቋ ማቅረብ እንደሚቻል ለማሳየት ነው። ከዚያ ጎን ለጎን እንቆቅልሾችን በኢምቋ የማቅረብ ልምድ እንድታዳብሩ ሲቀርብላችሁም የመተርጎም ብቃታችሁን ማሳደግ ነው።

የእንቆቅልሽ ጨዋታ የሚከተለው ዓይነት ሂደት አለው፤

ጠያቂው፤ "እንቆቅልህ?"

ተጠያቂ፤ "ምን አውቅልህ" ይላል

ቀጥሎ ጠያቂ እንቆቅልሹን ያቀርባል

**ምሳሌ አንድ:**

ጠያቂው፤ "እንቆቅልህ?"

ተጠያቂ፤ "ምን አውቅልህ" ይላል

ጠያቂ፤ *ከላይ ነፍስ የለም- ሞት ከታች ነፍስ የለም- ሞት መሃል ምን- ነፍስ ማዳን መቻል አለ ምን።* (ከላይ በድን፤ ከታች በድን፤ መሃሉ ነፍስ አድን)

ተጠያቂ፤ አክንባሎ፣ ምጣድና እንጀራ ነው።

ምሳሌ ሁለት፡

ጠያቂው፤ "እንቆቅልህ?"

ተጠያቂ፤ "ምን አውቅልህ" ይላል

ጠያቂ፤ *እናት ሆድ መውጣት እንደጋና እናት ራስ መርገጥ ምን (ከእናቷ ሆድ ወጥታ*

*እናቷን የምትረግጥ)*

**ተጠያቂ፤** የክብሪት እንጨት

## መልመጃ

**የሚከተሉትን እንቆቅልሾች መልስ በክፍል ውስጥ በኢምቁ ግለጹ**

1. **ኢ.ምቁ፡** *ጠዋት መሄድ ስንት እግር፣ አራት፤ ከሰዓት በኋላ መሄድ በሰንት እግር ሁለት፤ መሸ መሄድ ስንት እግር ሦስት- ምን?*

   አማርኛ፡ ጠዋት በአራት እግር፤ ከሰኣት በሁለት እግር ፤ ማታ በሦስት እግር የሚሄድ

2. **ኢ.ምቁ፡** *መዞር መዞር በኋላ በር መዝጋት ምን ቀጭን እንጨት- ምን?*

   አማርኛ፡ ዞሮ ዞሮ መዝጊያው ጭራሮ

3. **ኢ.ምቁ፡** *አይን ጥኩር መቀባት ኩ-ል ከዛ ገቢያ መሄድ ምን?*

   አማርኛ፡ አይኗን ተኩላ ገበያ የምትወጣ

4. **ኢ.ምቁ፡** ጽጉር ብጥር ብጥር ከዛ ገቢያ መሄድ- ምን?

   አማርኛ፡ ጸጉሯን አበጥራ ገበያ የምትወጣ

5. **ኢ.ምቁ፡** *አይን ብዙ አለ ግን ማየት አይደለም ምን?*

   አማርኛ፡ ብዙ አይኖች አሏት ግን አታይም።

# ክፍለ ትምህርት አራት

## የኢምቋ ሰዋሰው ናሙናዎች ልምምድ

**ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹የሙስና አስከፊነት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቋ አንብቡ።**

1. **ኢምቁ:** *ባንክ ዓለም ሙስና ትርጉም እንዴት- ሕዝብ ስልጣን ስጠ ያ ሰው ስልጣን ጥቅም ምን- ራስ ሀብታም ማድረግ።*

   **አማርኛ:** የዓለም ባንክ ሙስናን “በህዝብ የተሰጠ ስልጣንን ለግል ብልጽግና መጠቀም” በማለት ይተረጉመዋል።

2. **ኢምቁ:** *ሙስና ሀገር ህዝብ ሁለቱም መኖር ስጋት ከፍተኛ።*

   **አማርኛ:** ሙስና ለአንድ ሀገርና ህዝብ ህልውና ከፍተኛ ስጋት ነው።

3. **ኢምቁ:** *አስተዳደር መልካም የለም- ሠላም፣ ልማት፣ ዲሞክራሲ መምጣት ተስፋ ተስፋ አይቻልም*

   **አማርኛ:** መልካም አስተዳደር ከሌለ ደግሞ ሠላም፣ ልማትና ዴሞክራሲ ይረጋገጣሉ ተብሎ አይታሰብም።

4. **ኢምቁ:** *ሙስና ችግር ብዙ አንድ ሀገር እድገት ጉዳት- ሁለት ሀገር ስም ውጭ መበላሸት ።*

   **አማርኛ:** ሙስና የሀገርን እድገት ከመጉዳት በተጨማሪ የሀገርን ስም ያጠፋል።

5. **ኢምቁ:** *ሙስና ሰው ማየት ዝም ራሱ ሙስና ተመሳሳይ*

   **አማርኛ:** ሙሰኞችን አለማጋለጥ እራሱ ሙሰኝነት ነው።

# ምዕራፍ አራት

## ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ



**የሚጠበቁ ውጤቶች:**


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- ስለቤተሰብ ሕግ ምንነትና አስፈላጊነት በምክንያትና በውጤት አስደግፋችሁ በኢምቋ ታስረዳላችሁ፤
- ከቤተሰብ ሕግ ጋር የተያያዙ የኢምቋ ምልክቶችን ከነሥነምልክታዊ ውበታቸው በዕለት ተዕለት ተግባቦት ውስጥ ትጠቀማላችሁ፤
- ከምንባቡ ዋናና ዝርዝር ሐሳቦችን ትለያላችሁ፤
- ከአንድ ምልክት ተጨማሪ ምልክቶችን ትመሠርታላችሁ፤
- ለምልክቶች ተቃራኒ ትሰጣላችሁ፤
- የኢምቋ ግስ ዓይነቶችን ትዘረዝራላችሁ፤
- የግል ሐሳባችሁን ለመግለፅም ግሶቹን ትጠቀማላችሁ፤
- የግሶቹን ልዩነትነት በምሳሌ አስደግፋችሁ ታስረዳላችሁ፤


## ቁልፍ ምልክቶች



ሳይንስ




ሳይንቲስት




ዳሰሳ




ቴክኖሎጂ




ገላጭ




ዋሻ




ክህሎት




ግብአት




ትንቢቶች




ራዕይ




ማዕከል




ማደራጀት




መተንተን




እሴት




ተልዕኮን




ሽግግር




ግስ



ግልጽ



አመልካች




## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማነቃቂያተግባር

### እይታዊ ንባብ

1. የሚከተለውን ምስል በጥንቃቄ ተመልክታችሁ ምን እንደተረዳችሁ ለመምህራችሁ አስረዱ።
2. በምስሉ ላይ ስለሚታየው የኢንዱስትሪ ፓርክ የምታውቁት መረጃ ካለ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ።
3. ይህን አይነት ትላልቅ የኢንዱስትሪ ፓርኮች መገንባት ለሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ያለውን ጠቀሜታ አብራሩ።



የሀዋሳ የኢንዱስትሪ ፓርክ

## ቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. የአንደኛ ደረጃ ትምህርት ተማሪዎች ሆናችሁ ትጠቀሙበት የነበረው ወይም ሌሎች ሰዎች ሲጠቀሙበት የነበረው ዓይነት ሞባይል ዛሬ ከምትጠቀሙበት ልዩነት ያለው ይመስላችኋል?
2. የሳይንስና ቴክኖሎጂ መስፋፋት ለአንድ ሀገርና ህዝብ ያለው ጠቀሜታ ምንድነው?
3. ከቴክኖሎጂ ውጤቶች መካከል የሚያስደንቃችሁ የቴክኖሎጂ ውጤት ምንድነው? ኢትዮጵያ ያንን መስራት ያልቻለችው ለምን ይመስላችኋል?

## ምንባብ

ተማሪዎች፤መምህራችሁ ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሃሰቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቀቄ ተመልከቱ።

### ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ

ከጥንት ጀምሮ የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን ለማሻሻል ጥረት ሲያደረግ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ። የሰው ልጅ ገና በዋሻ በመኖር ላይ በነበረበት ዘመን በግል ጥረቱ የተለያዩ መሳሪዎችን መስራትና እንዴት መጠቀም እንደሚችል ተማረ።

ለሚሰራቸው ስራዎችም ቅደም ተከተል አዘጋጅቶ መከተል ጀመረ። በሂደትም ለኑሮው መሻሻል አስተዋጽኦ ማድረግ የሚችሉ ክንውኖችን እየፈጠረ ተግባራዊ ማድረግ ጀመረ። በአንድ ላይ ሲታዩ እውቀቱን፣ ክሂሎቱን፣ መሳሪያዎቹንና ግብአቶቹን የተጠቀመበትን ሁኔታ ዛሬ ቴክኖሎጂ ብለን የምንጠራውን ይወክላል።

ውክፔዲያ ሳይንስን "በተግባር ሊፈተኑ በሚችሉ ማብራሪያዎችና እንዲሁም ትንቢቶች መንገድ እውቀትን የሚገነባና የሚያደራጅ መዋቅር ነው" በማለት ይተረጉመዋል። ሳይንስን ከኃይማኖትና ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች የሚለየው አስተምሮው ሊፈተንና ሊረጋገጥ የሚችል መሆኑ ነው። ሳይንስ በአጠቃላይ መልኩ የሳይንሳዊ ዘዴ ተብሎ የሚታወቀውን የምርምር መንገድ ይከተላል። ቴክኖሎጂ ደግሞ የሳይንሳዊ ምርምሮች ውጤት ነው። ሳይንስ ቴክኖሎጂን ይፈጥራል ቴክኖሎጂ ደግሞ ሳይንስና ያዳብራል። ስለዚህ ሳይንስና ቴክኖሎጂ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ማለት ይቻላል።

ሁሉም ሀገሮች የሚንቀሳቀሱት የማደግና የመሻሻል ራዕይ ይዘው ነው። ይህን ራዕይ ለማሳካት ደግሞ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ቁልፍ ሚና አላቸው። ሀገራችን ኢትዮጵያም ተመሳሳይ ራዕይ ይዛ የምትንቀሳቀስ ሲሆን፣ ለተግባራዊነቱም ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት ልዩ ትኩረት ተስጥቶ እየተሰራ ነው። ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት በር የሚከፍቱ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን ከመክፈትና ከማስፋፋት በተጨማሪ ብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃዎች ማዕከልም አቋቁማለች። ዋና መቀመጫውን አዲስ አባባ፣ ልዩ ስሙ ቡልጋሪያ ማዞሪያ ያደረገው የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ ማዕከል (ሳ.ቴ.መ.ማ) በማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 257/2004 ተመስርቷል። ይህ ተቋም የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃዎችን በማፈላለግ፣ በመሰብሰብ፣ በመመምረጥ፣ በማደራጀት፣ በመተንተን እና በጥናትና ምርምር እሴት ጨምሮ በማሰራጨት የሀገሪቱን የቴክኖሎጂ ሽግግር ሂደት የማፋጠን ተልዕኮን ተስጥቶት የተመሰረተ ማዕከል ነው።

በዘርፉ የተጀመረው ጥረት ስኬታማ እንዲሆንም በ2004 ዓ.ም የኢትዮጵያ የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን ፖሊሲ ፀድቆ ወደ ስራ ተገብቷል። ፖሊሲው ሀገሪቷ ውጤታማ የሆኑ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን ለማፈላለግ፣ ለመምረጥ፣ ለማስገባት እንዲሁም ለመጠቀም የሚያስችላትን ሀገራዊ የኢኖቬሽን ስርዓት ለመፍጠር ያለመ ነው። የፖሊሲው ዓላማ ውጤታማ የሆኑ የውጭ ቴክኖሎጂዎችን በማፈላለግ፣ በመምረጥና በማስገባት በማምረቻና በአገልግሎት መስጫ ተቋማት ውስጥ የመማር፣ የማላመድና የመጠቀም ሀገራዊ አቅም ለመገንባት የሚያስችል የቴክኖሎጂ ሽግግር ማዕቀፍ መፍጠር ነው። በማዕከሉ በኩል የሀገሪቷን የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂ እና ኢኖቬሽን ችግሮች ጥናትና ምርጥ ተሞክሮ ያላቸው የሌሎች ሀገራት ሁኔታ ላይ የዳሰሳ ጥናት በመካሔድ ላይ ይገኛል። በዚህም መሠረት አስራ አንድ ወሳኝ የፖሊሲ ጉዳዮች ተለይተዋል። እነዚህም የቴክኖሎጂ ሽግግር፣ የሰው ሀብት ልማት፣ የማምረቻና የአገልግሎት ሰጪ ተቋማት፣ ምርምር፣ የፋይናንስ ሥርዓትና ማበረታቻ ሥርዓት፣ ብሔራዊ የጥራት መሰረተ ልማት፣ የዩኒቨርሲቲዎች፣ የምርምር ተቋማት፣ የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ተቋማትና የኢንዱስትሪ ትስስር፣ የአዕምሯዊ ንብረት ሥርዓት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃ፣ የአካባቢ ልማትና ጥበቃ እንዲሁም ዓቀም አቀፍ ትብብር ናቸው።

የፖሊሲውን አፈፃፀም ለመምራት፣ ለመደገፍና ለመከታተል ያስችል ዘንድ

ሀገራዊው የኢኖቬሽን ሥርዓት አስተዳደር መዋቅር ተዘርግቷል። የኢኖቬሽን ሥርዓቱ ዋና ዋና ተዋናዮችም ሀገራዊው የሳይንስና ቴክኖሎጂ ምክር ቤት፣ የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርና ሌሎች ሚኒስቴር መስሪያ ቤቶች እንዲሁም የኢኖቬሽን ድጋፍና የምርምር ሥርዓት ናቸው።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ወደ መካከለኛ ገቢ ካላቸው ሀገራት ተርታ ለመሰለፍ፣ በሂደትም የአደጉ ሀገሮችን ለመቀላቀል የሳይንስና ቴክኖሎጂ ሚና ወሳኝነት ታምኖበት ለእድገቱ ከፍተኛ ጥረት እየተደረገ ነው። ለዚህ ስኬት መስማት የተሳናቸው የራሳቸውን ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው የፈጠራ ውጤቶችን ለአለማችን ያበረከተው መስማት የተሳነው ሳይንቲስት ቶማስ ኤዲሰን ጥሩ ማስረጃ ነው። የኤዲሰን ታሪክ በአራተኛ ክፍል የኢ.ምቋ መማሪያ መጽሀፍ ውስጥ ይገኛል።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በክፍል ውስጥ በኢምቋ መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢ.ምቋ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢ.ምቋ አንብቡ።
2. የምንባቡን ጠቅላላ መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ወስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢ.ምቋ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢ.ምቋ አቅርቡ።

1. በምንባቡ መሠረት ሳይንስ ምንድነው?
2. ሳይንስን ከኃይማኖትና ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች የሚለየው ምንድነው?
3. ሳይንስና ቴክኖሎጂ የሚገናኙት እንዴት ነው?
4. ለሀገሮች የማደግና የመሻሻል ራዕይ መሳካት ቁልፉ ምንድናቸው?
5. ኢትዮጵያም የማደግና የመሻሻል ራእዩዋን እውን ለማድረግ ለሳይንስና ቴክኖሎጂ እድገት የወሰደቻቸውን እርምጃዎች ጥቀስ

6. የብሔራዊ የሳይንስና ቴክኖሎጂ መረጃዎች ማዕከል ተልእኮ ምንድነው?
7. የሀገራዊው የኢኖቬሽን ሥርዓት ዋና ዋና ተዋናዮችም እነማናቸው?

## መልመጃ ሦስት

### የምልክቶች ፍቺ እና ተቃራኒ ማሳየት

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች ፍቺና ተቃራኒ ጽንሰ ሃሳብ የያዙ ምልክቶችን በክፍል ውስጥ አሳዩ

1. ስኬት
2. ኋላቀርነት
3. ሳይንሳዊ
4. ብልጽግና
5. የጋራ

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## መልመጃ አንድ

ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ ከሚለው ምንባብ ውስጥ አምስት ግልጽ ግሶችን ለይታችሁ አውጡ። በመቀጠልም በአምስቱ ግሶች የራሳችሁን ዐረፍተ ነገሮች በመመሥረት በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ አሳዩ።

## መልመጃ ሁለት

ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ ከሚለው ምንባብ ውስጥ ግልጽ ግስ የያዙ አምስት ዐረፍተ ነገሮች ካወጣችሁ በኋላ የኢ.ምቋ ትርጉማቸውን ስጡ።

**ምሳሌ፡**

**ከምንባብ ውስጥ የወጣ ዐረፍተነገር**

ከጥንት ጀምሮ የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን ለማሻሻል ጥረት ሲያደረግ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ።

የተሰመረባቸው ምልክቶች ግልጽ ግሶች ናቸው

**የኢምቋ ትርጉሙ፡**

*ቆየ ማስረጃ አሳየ ምን- ሰው ዱሮ ዱሮ ጀመረ ሰው ራስ፣ አካባቢ ማሻሻል ማሻሻል ሙከራ ሙከራ ማድረግ ነበር።*

# ክፍል ትምህርት አራት

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ቃላት ምልክቶችን ወክለው የተቀመጡ ናቸው። በቃላቱ የተወከሉትን ምልክቶች በማጣመር አዳዲስ ምልክቶችን በመፍጠር በክፍል ውስጥ አሳዩ።

*ምሳሌ*

*ሙያ + ባለቤት = ባለሙያ*

*ሳይንስ + ዊ = ሳይንሳዊ*

1. ሥነ እና ምግባር
2. ግለሰብ እና ዊ
3. ጤና እና ኛ
4. አቅም እና ቢስ
5. ኋላ እና ቀርነት

## መልመጃ ሁለት

**በምዕራፍ ሦስት ውስጥ በተማራችሁት መሠረት የሚከተሉትን እንቆቅልሾች መልስ በክፍል ውስጥ በኢምቁ አስረዱ**

1. *ኢ.ምቁ:* *እናት ጥቁር ልጅ ልጅ ግን ነጭ ነጭ ምን?*
   **አማርኛ፡** እናትየዋ ጥቁር ልጆቿ ነጫጭ

2. *ኢ.ምቁ:* *ድምጽ መሎህ አንበሳ ተመሳሳይ መተኛት ጊዜ ሞተ ሰው ተመሳሳይ ምን?*
   **አማርኛ፡** ሲጮህ እንደ አንበሳ ሲተኛ እንደ ሬሳ

3. *ኢ.ምቁ:* *እግር አራት አለ ግን ወንዝ ማቋረጥ ማለፋ አይችልም ምን?*
   **አማርኛ፡** አራት እግር አለው ወንዝ የማይሻገር

4. *ኢ.ምቁ:* *አዞ ጥቁር ተመሳሳይ ጥምዝምዝ ጥምዝምዝ ምን?*
   **አማርኛ፡** ጥቁር አዞ ተጠማዞ

5. *ኢ.ምቁ:* *መሄድ ጊዜ አለ አገኝ መመለስ ጊዜ የለም ጠፋ ምን?*
   **አማርኛ፡** ስሄድ አገኘኋት ስመለስ አጣኋት

## መልመጃ ሦስት

ከተለያዩ ምንጮች 10 እንቆቅልሾች አሰባስባችሁ በክፍል ውስጥ በኢምቁ በማቅረብ የክፍል ጓደኞቻችሁ እንዲመልሱ አድርጉ

# ክፍለ ትምህርት አምስት

## የኢምቀ ናሙና ሰዋሰው

ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍተ ነገሮች በሙሉ ‹‹ሳይንስና ቴክኖሎጂን የማስፋፋት ፋይዳ›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተስማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቀ አንብቡ።

1. **ኢ.ምቀ፡** *ቆየ ማስረጃ አሳየ ምን- ሰው ዱሮ ዱሮ ጀመረ ሰው ራስ፣ አካባቢ መሻሻል መሻሻል ሙከራ ሙከራ ማድረግ ነበር።*

   **አማርኛ፡** ከጥንት ጀምሮ የሰው ልጅ ራሱንና አካባቢውን ለማሻሻል ጥረት ሲያደረግ እንደነበረ መረጃዎች ያሳያሉ።

2. **ኢ.ምቀ፡** *ሰው ሰው ዱሮ ዱሮ ገና መኖር መቆፈር ጉርጓድ ሰፊ ውስጥ- ያ ጊዜ ራስ ሙከራ ሙከራ መሳሪያ ልዩ ልዩ ስራ ስራ እንደገና መሳሪያ መጠቀም እንዴት እንዴት መቻል መማር።*

   **አማርኛ፡** የሰው ልጅ ገና በዋሻ በመኖር ላይ በነበረበት ዘመን በግል ጥረቱ የተለያዩ መሳሪዎችን መስራትና እንዴት መጠቀም እንደሚችል ተማረ።

3. **ኢ.ምቀ፡** *ሰው ሰው ስራ ልዩ ልዩ ተራ ተራ ዝግጅት አንድ መጀመሪያ ሌላ መቀጠል መከተል መጀመር።*

   **አማርኛ፡** ሰው ልጅ ለሚሰራቸው ስራዎችም ቅድመ ተከተል አዘጋጅቶ መከተል ጀመረ።

4. **ኢ.ምቀ፡** *ሳይንስ ትርጉም ምን- ተግባር ሙከራ ፈታና ትክክል ስህተት ማዋቅ መቻል ማወቅ መገንባት ከዛ ስርአት መስተካካል መስተካካል መስፋፋት ሙ-ያ።*

   **አማርኛ፡** ሳይንስ ማለት በተግባር ሊፈተኑ በሚችሉ ማብራሪያዎችና እንዲሁም ትንቢቶች መንገድ እውቀትን የሚገነባና የሚያደራጅ መዋቅር ነው።

5. **ኢ.ምቀ፡** *ሳይንስ አንድ ኃይማኖት እና ተመሳሳይ ሌላ ሌላ መለየት መንገድ ምን-*

*ሳይንስ ማስተማር ምን ሙከራ ትክክል ስህተት ማወቅ መቻል ማስተማር እሱ ብቻ በቃ።*

**አማርኛ፡** ሳይንስን ከኃይማኖትና ከሌሎች የዕውቀት ዘርፎች የሚለየው አስተምሮው ሊፈተንና ሊረጋገጥ የሚችል መሆኑ ነው።

# ምዕራፍ አምስት

## የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት



**የሚጠበቁ ውጤቶች**


ተማሪዎች ከዚህ ትምህርት በኋላ፤

- የተባበሩት መንግስታት ድርጅትን አጭር ታሪክና ተያያዥ ጉዳዮች ደረጃውን የጠበቀ ኢ.ምቋ በመጠቀም ታስረዳላችሁ፤
- ከርዕሱ ጋር የተያያዙ የኢ.ምቋ ምልክቶችን በተለያዩ ምሳሌዎች ውስጥ ከነ ሥነምልክታዊ ውበታቸው ትጠቀማላችሁ፤
- ገላጭ ግሶችን በግል ንግግራችሁ ውስጥ በትክክለኛው መንገድ መጠቀም ትጀምራላችሁ፤
- የኢ.ምቋ ምልክቶችን በማጣመርና ሌላ ምልክት በመፍጠር ሀሳባችሁን ለማስተላለፍ ትጠቀማላችሁ፤
- ጥምር ምልክቶችን በመለያየት አዳዲስ ምልክቶችን ትሰራላችሁ፤
- የአፍሪካ ኅብረትን በተመለከተ መረጃዎችን አሰባስባችሁ በማጠናቀር በክፍል ጓደኞቻችሁ ፊት ታቀርባላችሁ፤


## ቁልፍ ምልክቶች



የተባበሩት መንግስታት ድርጅት




መመስረት



ማርቀቅ



ግዙፍ




ደህንነት




ሰብዓዊ




ጣልያን



ዕልቂት



ህልውና




ትምክህተኞች



ማክተሚያ




ጀርመን




አቅም መክዳት



ፋሽስት




እብሪት




ግፍ



ዳተኝነት




እንዳሻቸው




ሐይ ማለት/ማስቆም




መሳን




መፈረካከስ




ናዚ




ጃፓን




ውድመት


መዳኘት


ማፅናት


መጎትጎት


ምጣኔ-ሐብታዊ

## ክፍለ ትምህርት አንድ

### ማነቃቂያ ተግባር

### እይታዊ ንባብ

ከታች የተቀመጠውን ፎቶ በጥንቃቄ ተመልከቱና የሚከተሉትን ጥያቄዎች በኢ.ምቋ መልሱ

1. ጽህፈት ቤቱ የሁሉም መንግስታት መሆኑን የሚያሳየው ምንድነው?
2. ከሚታዩት ባንዲራዎች ውስጥ የሚወክለውን ሀገር የምታውቁት ካለ ጥቀሱ



ኒወርክ የሚገኘው የተባበሩት መንግስታት ጽህፈት ቤት

## የቅድመ ምንባብ ጥያቄዎች

1. ከዚህ በፊት የተበባሩት መንግስታት ድርጅትን በተመለከተ ያያችሁትን ወይም ያነባችሁትን መረጃ ለክፍል ጓደኞቻችሁ አካፍሉ። ለምሳሌ ድርጅቱ በአካባቢያችሁ ያከናወነው ወይም እያከናወነው ያለው የበጎ አድራጎት ሥራ ካለ ወይም ከመገናኛ ብዙኃን ያገኛችሁት መረጃ ካለ ልትገልጹ ትችላላችሁ።
2. የሀገሮች መተባበር ለዓለማችን ያለውን ጠቀሜታ አስረዱ።

## ምንባብ

መምህራችሁ **የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት** የሚለውን ምንባብ ሲያነቡ ሃሰቡን ለመረዳት ከመሞከር ጎን ለጎን የምልክት አጠቃቀማቸውን በጥንቃቄ ተመልከቱ።

### የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የተ.መ.ድ.) የተመሠረተው በ54 ሀገራት ነው። ከመሥራች ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ነች። በአሁኑ ጊዜ የአባል ሀገሮች ቁጥር ወደ 193 ደርሷል። በዚህ ምክንያትም የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለማችን እጅግ ግዙፉና ታላቁ ድርጅት ነው። ዋና ቢሮዎቹ የሚገኙት በኒወርክና በጄኔቫ ሲሆን በአለም ዙሪያም ብዙ ቅርንጫፍ ቢሮዎች አሉት።

የተ.መ.ድ ዋና ዓላማ ለዓለማችንና ለሰው ልጆች ይጠቅማሉ ተብለው የታመነባቸውን ግቦች ለማሳካት ሀገራት በጋራ እንዲሰሩ ማስተባበርና መምራት ነው። እነዚህም የሚከተሉት ናቸው፤ ዓለም አቀፍ ሕግ መውጣትና በሥራ ላይ መዋል፣

ዓለምአቀፍ ደህንነት መከበር፣ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ማስመዝገብ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር ናቸው።

የተ.መ.ድ ከመቋቋሙ በፊት ሌላ ዓለምአቀፍ ድርጅት የነበረ ሲሆን ስሙም ሊግኦፍኔሽን ወይም የመንግስታቱ ማኅበር ይባል ነበር። የመንግስታቱ ማኅበር የተመሰረተው የ1ኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ላይ ነው። ከዚህ አስከፊ ጦርነት ማብቃት በኋላ ዓለማችን ዳግም ወደዚያ ዕልቂት እንዳትመለስ በማሰብ 54 አገሮች የመንግስታቱ ማኅበር የተሰኘውን ዓለምአቀፋዊ ተቋም መሰረቱ። ሆኖም ይህ ድርጅት የታሰበለትን ዓላማ ሊያሳካ አልቻለም። በተለይ ወደ ሕልውናው ማክተሚያ ላይ ለተቋቋመበት ታላቅ ዓላማ በፅናት የሚቆምበት አቅም ከዳው። እንደ ዓለምአቀፋዊነቱ ጠንካራና ፍትሐዊ መሆን አልቻም። ለምሳሌ ያህል ከመስራች ሀገራቱ አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያ በፋሺስት ጣልያን የግፍ ወረራ ሉአላዊነቷ ሲደፈር በተሰጠው ስልጣን መሠረት መዳኘት ሲገባው ዝምታና ዳተኝነትን መረጠ። ከዚህ አልፎም ኢትዮጵያ ጉዳዩን እንዲያይላት ስትጠይቅ፣ የተሰጣት ፍርድ ፍትሃዊ አልነበረም። ብዙ ሀገራት በድርጅቱ ላይ እምነት እያጡ ጠንከር ያሉትም እየናቁት መጡ። ጉልበተኞች፣ ዕብሪተኞች፣ ትምክህተኞች እንዳሻቸው ሲሆኑ ሊጉ ሐይ ማለት ተሳነው። ዓላማውንም ስቶ መፈረካከስ ጀመረ። የጀርመን ናዚዎች፣የጣሊያን ፋሽስቶችና የጃፓን ወራሪዎች ሦስትዮሽ የአክሲስ ተጣማሪዎች በሊግኦፍኔሽንስ ድክመትና መፈረካከስ ተንተርሰው ምድራችንን ወደ 2ኛው የዓለም ጦርነት ከተቷት። ይህ ጦርነት በታሪክ ከዛ በፊትም ሆነ በኋላ ታይቶ የማይታወቅ የሰው ዕልቂትና የንብረት ውድመት አስከተለ።ወደ የ2ኛው የዓለም ጦርነት መደምደሚያ ላይ አክሲሶቹ ወደማይቀረው ሽንፈታቸው ሲቃረቡ፣ ዓለምን ከዚያ ዓይነቱ ጥፋት፣ውድመትና ምስቅልቅል የሚጠብቃት የሁነኛ ዓለምአቀፋዊ ድርጅት ማቋቋሚያ ሃሳብ ተጠነሰሰ። በመጨረሻም የዛሬው የተ.መ.ድ. ተመሰረተ።

የዓለም ሰላምና ደህንነትን ማፅናትን ቀዳሚው በማድረግ ማኅበረ-ምጣኔ ሐብታዊ ልማትና የሰብዓዊ መብት ከበሬታን ማስፈን የተ.መ.ድ. ምሶሶዎች ናቸው።ድርጅቱ ከተመሰረተ አንስቶ ታላላቅ የሰላም ማስከበርና የሰብዓዊ ዕርዳታ ስራዎችን ሲያከናውን ቆይቷል።አሁንም በዚሁ እንደገፋበት ነው። ይህም ሆኖ እንከኖች እንዳሉበት እየጠቆሙ የሚወቅሱትና እንዲስተካከል የሚጥሩ አሉ።የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በታዛቢዎቹ ዘንድ በተለያዩ ፅንፎች ይታያል።በአንድ ወገን ድርጅቱ ለዓለም ሰላምና ሰብዓዊ ልማት ሁነኛ ተደርጎ ይቆጠራል።ሌሎች ደግሞ ውጤት የራቀው በሙስና የተተበተበና አድሏዊነት የሞላው አድርገው የሚያዩት አሉ።

እጅግ ከበዙት ድክምቶቹ አንዱ ከ22 ዓመታት በፊት በሩዋንዳ በጥቂት ወራት ውስጥ ከ800 ሺህ ያላነሱ ሰዎች ያለቁበትን የዘር ፍጅት ለማስቆም የረባ ጥረት አለማድረጉ ነው። ከ2ኛው የዓለም ጦርነት ወዲህ የዓለም ሰላምና ደህንነት ጉዳይ በተለይም ለ5ቱ ሃያላን አድራጊ-ፈጣሪነት የተተወ መሆኑ የለውጥ ጥያቄ አስነስቷል። በተለይም የደቡባዊ ንፍቀ ክበብ አገሮች የድርጅቱ ጠቅላላ ጉባኤ ጉልህና ወሳኝ ድምፅ እንዲኖረው ሆኖ እንዲሻሻል እየጎተጎቱ ነው።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉት ጥያቄዎች ምንባቡን በተሻለ ሁኔታ ለመረዳት እንዲያግዛችሁ ታቅደው የተዘጋጁ ስለሆኑ በክፍል ውስጥ በኢምቂ መልሱ።

1. በዚህ ምዕራፍ የመጨረሻ ክፍል ከፍ ሲል ከተነበበላችሁ ምንባብ ተወስደው ወደ ኢምቂ የተተረጎሙ ዐረፍተ ነገሮች ተቀምጠዋል። የኢምቂ ዐረፍተ ነገሮቹን በሚገባ ካጠናችሁ በኋላ፣ ከምንባቡ ውስጥ አንድ ዐረፍተ ነገር ወይም አንድ አንቀጽ ወስዳችሁ በኢምቂ አንብቡ።

2. መጽሀፎቻችሁን ሳትመለከቱ የምንባቡን መልእክት በአጭሩ በራሳችሁ አቀራረብ በክፍሉ ውስጥ አቅርቡ።

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ጥያቄዎች የምንባቡን ሐሳብ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለመመዘን የቀረቡ ናቸው። ጥያቄዎቹን በትክክል ለመመለስ መሞከራችሁ በዓይን የመስማት ብቃታችሁንም ለማዳበር ይረዳችኋል። ስለዚህ መምህራችሁ ጥያቄዎቹን በኢምቂ ሲያነቡላችሁ በጥንቃቄ ተመልከቱና፣ ተገቢ መልሶችን በኢምቂ አቅርቡ።

1. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የተቋቋመበት ዋንኛ ዓላማ ምንድነው?
2. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለማችን ግዙፉና ታላቁ ድርጅት ነው የሚባለው ለምንድነው?
3. ኢትዮጵያን ምሳሌ በማድረግ ሊግኦፍኔሽን ወይም የመንግስታቱ ማኅበር ጠንካራና

   ፍትሐዊ እንዳልነበረ አስረዱ።
4. የሊግኦፍኔሽን ወይም የመንግስታቱ ማኅበር ድክመት ያስከተለው ዋንኛ ታሪካዊ ክስተት ምን ነበር?
5. በዓለማችን ከተነሱ ጦርነቶች ሁሉ የ2ኛውን የዓለም ጦርነት አስከፊ የሚያደርገው ምንድነው?
6. 2ኛው የዓለም ጦርነት ለተባበሩት መንግስታት መመሥረት መነሻ የሆነው እንዴት ነበር?
7. የተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከሚወቀስባቸው ድክመቶች አንዱ የሆነውና በአፍሪካ ውስጥ የተከሰተውን አሳዛኝ ታሪክ አስረዱ።

# ክፍለ ትምህርት ሁለት

## ገላጭ ግሶች

**ገላጭ ግሶች:** እነዚህ ግሶች ምስሳዊ ሲሆኑ ግሶቹ እንደሚወክሉት ነገር የሚለዋወጡና ቋሚ የሚባል የእጅ ቅርጽም ሆነ አቅጣጫ የሌላቸው ግሶች ናቸው። ቅርጻቸውም ሆነ አቅጣጫቸው በዐረፍተ ነገሩ ውስጥ እንዳላቸው አገባብ ሊለዋወጥ የሚችል ነው። ሆኖም እንደአመልካች ምልክቶች መልእክቱ ወደ የሚመለከተው አካል የማመልከት ባህሪ የላቸውም።


**ምሳሌዎች:** *መቆም፣ መውሰድ፣ መምታት፣ መጓዝ፣ መንዳት፣ መጫወት፣ መፈለግ፣ ማጥፋት፣ ወዘተ*

### አጠቃቀም

**ምሳሌ አንድ: *መቆም***

1. *መኪና መቆም ክልክል።* (መኪና ማቆም ክልክል ነው።)
2. *ሰው መቆም ነውር።* (ሰው ማቆም ነውር ነው።)
3. *ሥራ መቆም ሕግ ቅጣት።* (ሥራ ማቆም ሕግ ያስቀጣል።)

**መቆም** እንደ አገባቡ ሦስት የተለያዩ ምልክቶች ይጠቀማል። የመቆም መሠረታዊ ምልክት የሚከተለው ነው ነገር ግን ይህ ምልክት የሚሰራው በሦስተኛው ዐረፍተ ነገር ውስጥ ብቻ ነው፤



**መቆም/ማቆም**

*ምንጭ የኢ.መ.የ.ብ.ማ. መዝገበ ምልክት*

በቁጥር አንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የእጅ ቅርጹ  ቅርጽ ሲሆን ቅርጹ እንደ መኪናው አቋቋምና አቅጣጫ በአጅ ላይ ያርፋል። በቁጥር ሁለት ዐረፍተ ነገር ውስጥ ግን ቅርጹ 2 ቁጥር

ቅርጽ ሲሆን ተገልብጦ በመዳፍ ላይ ይቆማል።

**ምሳሌ ሁለት፡ መውሰድ**

1. ምግብ መውሰድ
2. እቃ ከጠረጴዛ ላይ መውሰድ
3. ልጅ ትምህርት ቤት መውሰድ
4. መድሀኒት መውሰድ
5. አንድን ነገር ከአንድ ቦታ ወድ ሌላ ቦታ መውሰድ

የመውሰድ ምልክት በአምስቱ ዐረፍተነገሮች ውስጥ የተለያየ ምልክቶች አሉት።

**ምሳሌ ሦስት፤መምታት**

መምታት እንደአገባቡ ገላጭ ወይም አመልካች ግስ ሊሆን ይችላል። በአንድ ጊዜ ሁለቱንም የሚሆንበት አገባብም አለ። እንደ መስጠት ከተናጋሪ ወደ ውጭ ወይም ከውጭ ወደ ተናጋሪው በመሄድ መቼና ተመቺን ከማሳየት በተጨማሪ ምልክቱ እንደ መምታቱ አይነትና ምቱ እንደ አረፈበት ቦታ ሊለያይ ይችላል።

ምሳሌ

1. *ጫላ ዱላ መምታት* (የዱላ አያያዝ እግር ላይ ሲያርፍ ያሳያል)   (ጫላ እግሬን በዱላ መታኝ።)

በዚህ የኢ.ምቋ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚታዩት ምልክቶች ሦስት ብቻ ናቸው፤ የጫላ ምልክት፣ የዱላ ምልክትና የመምታት ምልክት። የመምታት ምልክት ወደ እግር የሚጠቁም ከመሆኑም በላይ የእጅ ቅርጹ ዱላ የጨበጠ እጅ አይነት ሆኖ እንቅስቃሴው እንደ አመታቱ ጥንካሬ ይለያያል። ግሱ ድርጊቱን እንደ ድራማ ስለሚያሳይ ተመልካቹ  የተመታው አካል እግር መሆኑና አመታቱ እንዴት እንደነበረ በቀላሉ መረዳት ይችላል።

2. *ሐጎስ ቦክስ መምታት* (ሐጎስ በቦክስ መታኝ።)

በዚህ ዐረፍተ ነገር ውስጥ የመምታት የእጅ ቅርጹና ቅርጹ የሚያርፍበት ቦታ በመጀመሪያው ምሳሌ ውስጥ ከሚታየው ይለያል። በቦክስ መታኝ ቅርጹ የተጨበጠ እጅ ሲሆን ቅርጹ የሚያርፈው ቦክሱ ያረፈበት ቦታ ነው። በጥፊ መታኝ ከሆነ ደግሞ የእጅ ቅርጹ የተዘረጋ መዳፍ ይሆናል። በቦክስ መታኝ እና በጥፊ መታኝ በአንድ የአመልካች ግስ ምልክት ይገለጻሉ።

## መልመጃ አንድ

የሚከተሉትን ጥያቄዎች በምሳሌ እያስደገፋችሁ በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ መልሱ

1. የኢ.ምቋ ገላጭ ግስ ማለት ምን ማለት ነው?
2. የኢ.ምቋ ገላጭ ግሶች ልዩ መለያ ምንድነው?
3. የኢ.ምቋ ገላጭ ግሶች ከግልጽ ግሶች የሚለዩት በምንድነው?

## መልመጃ ሁለት

የሚከተሉት ገላጭ ግሶች እንደ አገባባቸው ሊለዋወጡ እንደሚችሉ ከላይ በምሳሌዎች ውስጥ እንዳያችሁት የኢ.ምቋና የአማርኛ ዐረፍተ ነገሮች ውስጥ በመጠቀም በክፍል ውስጥ አሳዩ።

1. መንዝ
2. መንዳት
3. መጫወት
4. መፈለግ
5. ማጥፋት

## መልመጃ ሦስት

ከምንባቡ ውስጥ አምስት ገላጭ ግሶችን ፈልጋችሁ በማውጣት የራሳችሁን ዐረፍተ ነገሮች መሥርቱ።

ምሳሌ፡

**መምራት**

## ክፍለ ትምህርት ሦስት

### መረጃ ማሰባሰብ፣ ማጠናከርና በክፍል ውስጥ ማቅረብ

ኢ.ትዮጵያ በአፍሪካ ሕብረት ምስረታ ውስጥ ያደረገችውን አስተዋጽኦ ከተለያዩ መረጃዎች በማሰባሰብ ሪፖርት ካዘጋጃችሁ በኋላ በክፍል ውስጥ በኢ.ምቋ አቅርቡ።

# ክፍለ ትምህርት አራት

## የኢምቋ ናሙና ሰዋሰው

**ከዚህ በታች የተቀመጡት አማርኛ ዐረፍ ተነገሮች በሙሉ ‹‹የተባበሩት መንግስታት›› ከሚለው ምንባብ ውስጥ የተወሰዱ ናቸው። ናሙናዎቹን በጥንቃቄ ከተለማመዳችሁ በኋላ ወደ ምንባቡ በመመለስ በኢምቋ አንብቡ።**

1. **ኢ.ምቋ፡** *መተባበር መንግስት መመስረት ሀገራት ሰንት 54።*

   **አማርኛ፡** የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት (የተ.መ.ድ.) የተመሠረተው በ54 ሀገራት ነው።

2. **ኢ.ምቋ፡** *መተባበር መንግስት መመስረት ልዩ ልዩ ሀገራት አንድ ኢትዮጵያ።*

   **አማርኛ፡** ከተባበሩት መንግሥታት ድርጅት መሥራች ሀገራት መካከል አንዷ ኢትዮጵያ ነች።

3. **ኢ.ምቋ፡** *መተባበር መንግስት ዓለም ሁሉ ድርጅት በላይ ትልቅ ትልቅ ድርጅት።*

   **አማርኛ፡** የተባበሩት መንግስታት ድርጅት የዓለማችን እጅግ ግዙፉና ታላቁ ድርጅት ነው።

4. **ኢ.ምቋ፡** *መተባበር መንግስት ዓላማ ምን-ምን- አንድ ሕግ ዓለም ማቀፍ ዝግጅት መፈጸም፣ ሁለት ዓለም ደህና መጠበቅ፣ ሦስት ዓለም ሁሉ ኢኮኖሚ ማህበር ማደግ መምጣት፣ አራት ሰው ሁሉ መብት መከበር እኩል።*

   **አማርኛ፡** የተ.መ.ድ ዋንኛ ዓላማ ዓለም አቀፍ ሕግ ማውጣትና መተግበር፣ ዓለምአቀፍ ደህንነት መከበር፣ ዓለምአቀፍ የኢኮኖሚና ማህበራዊ ዕድገት ማስመዝገብ፣ የሰብዓዊ መብት መከበር ናቸው።

5. **ኢ.ምቋ፡** *መተባበር መንግስት ታዘበ ዓይን ማየት ልዩ ልዩ መንገድ ተመሳሳይ አይደለም።*

**አማርኛ፡** የተባበሩት መንግስታት ድርጅት በታዛቢዎቹ ዘንድ በተለያዩ ፅንፎች ይታያል።